# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 038 ጥቅምት 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

# «ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን የመዋደድና የመተሳሰብ ዓርማ ልናደርገው ይገባል»

አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ
የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን የመዋደድ፣ የመከባበርና የመተሳሰብ ዓርማ ልናደርገው ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ፡፡

15ኛው ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን «ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሃነታችን መገለጫ የሉአላዊነታችን ምሰሶ» በሚል መሪ ቃል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ተከብሯል፡፡

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ባስተላለፉት መልዕክት፤ ሰንደቅ ዓላማ አንዱ አገር ከሌላው የሚለይበት፣ የሌላው ተቀጥላ ወይም ተገዥ አለመሆኑን የሚያረጋገጥበት የነፃነት፣ የሉአላዊነት፣ መገለጫ ነው፡፡ የሰንደቅ ዓላማ ታሪክ የአንድ አገር የታሪክ ውጤት ነው፡፡

«ብሔራዊ ሰንደቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ችላ ምርቶቿን ለዓለም ገበያ የምታቀርብበት ጊዜ ተቃርቧል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አገራችን የምግብ ዋስትናዋን አረጋግጣ በዓለም ገበያ በምርቶቿ መሳተፏ የሩቅ ጊዜ ህልም ሳይሆን፣ እየቀረበ የሚገኝ የጥረት ውጤት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በክላስተር የለማ የአኩሪ አተር ሰብል ማሳን ጎብኝተዋል።

በአማራ ክልል ምርታማነትን ለማሳደግ በሚካሄደው ርብርብ፣ አኩሪ አተርን ለማምረት ሰፊ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በ38 ሺህ ሄክታር ላይ ያረፈውን የኩታ ገጠም ምርት እና በጠገዴ ወረዳ አዲስ ዓለም በኩታ ገጠም አንድ ሺህ 200 ሄክታር ላይ የተመረተውን አኩሪ አተር መመልከታቸውን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በምግብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የተጋረጠብንን አደጋ በመመከት ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገን የምንሰቅል ዜጎች መሆናችንን እናሳይስን

**ውብሸት ሰንደቁ**



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

አቶ ጃንጥራር አባይ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያዊነት አንድነት በመፅናት የተጋረጠብንን አደጋ በመመከት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ላለማስደፈር በየትኛውም ጊዜ መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ሆነን ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገን የምንሰቅል ኩሩ ኢትዮጵያውያን መሆናችንን ማሳየት ይኖርብናል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ገለጹ፡፡ የከንቲባ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች «ሰንደቅ ዓላማ የብዝኃነታችን መገለጫና የሉአላዊነታችን ምሰሶ ነው» በሚል መሪ ሃሳብ 15ኛውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን አክብረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ በመድረኩ ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ መላው ሕዝብ በኢትዮጵያዊነት አንድነት በመፅናት እና የተጋረጠብንን አደጋ በመመከት የአገራችንን ሉአላዊነት ላለማስደፈር በየትኛውም ጊዜ

የተጋረጠብንን አደጋ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service


## መንግሥት በትግራይ ክልል የሚገኙ አየር ማረፊያዎችና የፌዴራል ተቋማትን እንደሚጠብቅ አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት የአገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ሲል በትግራይ ክልል የሚገኙ አየር ማረፊያዎችንና የፌዴራል መንግሥት ተቋማትን መጠበቅ የግድ አስፈላጊ መሆኑን ገለጸ። ሕዝቡና የእርዳታ ሠራተኞች ራሳቸውን ከአሸባሪው ሕወሓት ወታደራዊ ተቋማት እንዲያርቁም ጥሪ አቅርቧል፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በሰሜን ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የመከላከል ርምጃ በተመለከተ ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳመለከተው፤ አሸባሪው ሕወሓት በሙሉ ዐቅሙ ጥቃት ከመክፈቱ በፊት የኢትዮጵያን የአየር ክልል በውጭ ጠላቶች ሲያስደፍር ቆይቷል። በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ መንግሥት የአገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ አስገድዶታል። በመሆኑም በትግራይ ክልል የሚገኙ አየር ማረፊያዎችንና የፌዴራል መንግሥት ተቋማትን መጠበቅ የግድ አስፈላጊ ነው ብሏል፡፡

መንግሥት በትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ገጽ 4

## የዓባይ ግድብ የነገዋን ኢትዮጵያ ዛሬ ለመገንባት መሰረት የሚጥል መሆኑን የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች ገለጹ

- ግድቡን ለፍጻሜ ለማብቃት በትብብር ይሠራሉ

# ከተማዋን የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ የሆቴሎችን አገልግሎት አሰጣጥ ማሳደግ ይገባል

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻ ማዕከል ለማድረግ የሆቴሎችን ሆስፒታሊቲ ማሳደግ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡ ቢሮው ከናሽናል ሪሰርች ኮንሰልታንሲ ኢንስቲትዩት እና ከአዲስ አበባ የሆቴል ባለንብረቶች ጋር በመተባበር ከ100 ባለኮከብ ሆቴሎች ለተውጣጡ ከ700 በላይ ባለሙያዎች የመጀመሪያው ዙር የሥራ ላይ ሥልጠና ሰጥቷል።

በሥልጠናው ላይ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ደስታ ሎሬንሶ እንደተናሩት፤ ባለፉት ዓመታት አገራዊ ሁኔታዎችና ኮሮና ቫይረስ የሆቴል እና ሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪውን የጎዱ ቢሆንም መንግሥት ለዘርፉ ከሰጠው ትኩረት አንጻር በወሰዳቸው እርምጃዎች ጉዳቱን መቀነስ ተችሏል።

ቱሪዝም ለልማትና እድገት ወሳኝ ምሰሶ በመሆኑ ተከታታይነት ያላቸው የቱሪዝም ሥራዎችን በማከናወን ዘርፉን ማነቃቃት እንደሚገባም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ መዲና፣ የአፍሪካ እና የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ የሆነች አዲስ አበባን ዋነኛ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ሰፋፊ የከተማ የልማት ፕሮጀክቶች ለከተማዋ የልማት ከፍታና ለቱሪዝም ልማት እገዛቸው የላቀ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ከተማዋ ብዙ የታሪክ፣ የባህል፣ የተፈጥሮ እና የመልካ ምድር ሀብቶቿን በአግባቡ በመጠቀም የቱሪዝም




መዳረሻዎች ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ የቱሪዝም አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና መስተንግዶ በማሻሻል ተወዳዳሪ ማድረግ ተገቢ መሆኑንም ዶክተር ደስታ አመላክተዋል።

በዚህም ረገድ የአዲስ አበባ የሆስፒታሊቲ ኢንዱስትሪ እና የሆቴሎች አገልግሎትን ማሻሻል እና በሙያ ብቁ ማድረግ ለከተማዋ ቱሪዝም ምቹና ተወዳዳሪ የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

ለሆቴል ባለሙያዎቹ የተሰጠው ሥልጠና በከተማችን ሰፊ የቱሪዝም ዕድሎችን ለማየት እና ለማስተዋወቅ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፣ የቱሪዝም ዘርፉንም በአዲስ ዕይታ እና በአዲስ ትኩረት የሚሠራበት መሆኑን ጠቁመዋል።

በተለያዩ የምግብ ዝግጅት፣ በሀይጂን፣ በአገልግሎት አሰጣጥ መስተንግዶ ላይ ክህሎታቸውን የሚያሳድግ የሦስት ቀን ሥልጠና የተሰጠ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ተመራቂዎቹ በየተቋማቸው ብቁ አገልግሎት እና ሙያዊ መስተንግዶ በመስጠትና የቱሪዝም አምባሳደር በመሆን የከተማዋን ገጽታ የሚለውጡ ናቸው ብለዋል።

ሥልጠናውን በማስተባበር እና በመደገፍ የአዲስ አበባ ሆቴል ባለንብረቶች ማህበር፣ ብሔራዊ ምርምርና ማማከር ፈርስት ኮንሰልታንት እና ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን እና ሰልጣኞችን በመላከ ለተባበሩ ሆቴሎች ምስጋና አቅርበዋል።

በአዲስ አበባ የሆቴል ባለንብረቶች ንግድ ዘርፍ ማህበር ፕሬዚዳንት ወይዘሮ አስቴር ሰለሞን በበኩላቸው፣ ሥልጠናው የአገራችንንና የከተማዋን እንግዳ ተቀባይነት በማሳደግ በቀጣይ ከተማዋ የምታዘጋጃቸው ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች መኖራቸውን ጠቁመው ሰልጣኞች ከወዲሁ እንዲዘጋጁ አሳሰበዋል።

የከተማችን ሆቴሎች በሰው ኃይል ማሳደግና ሆስፒታሊቲውን በማጠናከር ተወዳዳሪ ማድረግ የሆቴል ኢንዱስትሪውን የሚያሳድግ ነው ብለዋል።

የናሽናል ኢንቨስትመንት ግሩፕ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገዘኸኝ ብሩ በበኩላቸው ስልጠናው ከመጀመሩ በፊት ከአዲስ አበባ 30 ሆቴሎችን ከአዳማና ከቢሾፍቱ ስድስት ሆቴሎች ላይ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት መሠረት የተጀመረ መሆኑን አስታውሰዋል።

ሥልጠናው ሆቴሎች እርስበራስ ብቻ ሳይሆን በኢንዱስትሪው ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል ያሉት አቶ ገዛኸኝ፤ ከእንግዳ ጋር በቀጥታ የሚገናኘውን ሠራተኛ ክህሎትና አቀራረብ በማሳደግ እና የነበረውን ልምድ ለመለዋወጥ ያስቻለ ነው ብለዋል።

# ተቋማት የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ከማዘመን ባለፈ ለሳይበር ደህንነት ትኩረት እንዲሰጡ ተጠየቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ለማዘመን ከሚሠሩት ሥራ ጎን ለጎን ለሳይበር ደህንነት ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ(ዶ/ር) ጥሪ አቀረቡ፡፡

ዶክተር መኩሪያ ኃይሌ የ3ኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር አካል የሆነና የተቋማትን የሳይበር ተጋላጭነት መቀነስ ላይ ያተኮረ ውይይት መድረክ ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንዳሉት፤ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን ለማዘመን ከሚሠሩት ሥራ ጎን ለጎን ለሳይበር ደህንነት ትኩረት በመስጠት በአሠራር ሥርዓት፣ በቴክኖሎጂ እና ብቁ የሰው ኃይል በመመደብ ረገድ የበኩላቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል።

አገራችን አምራች የሆነ የሰው ኃይሏን በመጠቀም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንድታሳይ ወጣቱን ትውልድ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት እና ፈጠራ ላይ ብቃት እንዲኖረው ከማድረግ ባለፈ የሳይበር ደህንነት ግንዛቤውና አቅሙ እንዲዳብር በየደረጃው ካሉ ባለድርሻ አካላት ጋር መሥራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡

አብዛኛዎቹ የአገራችን ተቋማትም ሥራቸውን በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ አገልግሎታቸውን ከማዘመን ባሻገር የቴክኖሎጂውን ደህንነት ለመጠበቅና ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን ለመከላከል የሚያደርጉት ጥረት እጅግ አነስተኛ መሆኑ አደጋው የሚያደርሰውን ጉዳት የከፋ እንደሚያደርገው ገልጸዋል፡፡

የተቋማትን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ የተቋማት ኃላፊዎች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት መምራት እንዳለባቸው ጠቁመው፤ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት የተዘጋጀውን የሳይበር ደህንነት ወር እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተቋማት የአመራሮቻቸውንና ሠራተኞቻቸውን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ለማሳደግ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) ም/ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ትዕግስት ሃሚድ በበኩላቸው፤ ተቋማት ወደ ውስጣቸው በመመልከትና ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ የሚያዳርጓቸውን ጉዳዮችን በመለየት ክፍተቶችን የመድፈን፣ የባለሙያዎችን የሳይበር ግንዛቤ አቅም በማሳደግና በጋራ በመስራት የኢትዮጵያን የሳይበር ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡

ተቋማት ላይ የሚፈጸም የትኛውም ዓይነት የሳይበር ጥቃት በተቋሞቻችን ላይ ከሚያደርሰው የስም ማጥፋት፣ የገቢ መቀነስና ኪሳራ ባሻገር እስከመጨረሻውም ሊያሳጣን ይችላል ያሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ የሚጠቀሙባቸው ቴክኖሎጂዎች እና የአሠራር ሥርዓታቸውን ማዘመን፣ የቁጥጥር እና ክትትል ሥርዓታቸውን ማስፋት፣ ዘመኑን የሚመጥን በማድረግ በአገር ላይ ሊደርስ የሚችልን የሳይበር ጥቃት መከላከል እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

3ኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ወር ሲከበርም ተቋማት ወደ ውስጥ በመመልከትና ለሳይበር ተጋላጭነት የሚዳርጉ ጉዳዮችን በመለየት ክፍተቶችን የመድፈን፣ የባለሙያዎችን የሳይበር ግንዛቤ አቅም በማሳደግና በጋራ በመሥራት የኢትዮጵያን የሳይበር ሉዓላዊነት ማስጠበቅ ላይ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

3ኛው አገር አቀፍ የሳይበር ደህነት ወር «የተቀናጀ የሳይበር ደህነት ለአገር ሉአላዊነት» በሚል መሪ ቃል ከጥቅምት አንድ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም በመከበር ላይ መሆኑ ይታወቃል።



# የካፒታል ገበያን ለመደገፍ የሚያስችል ሥራ ተጀመረ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ አዲስ የተጀመረውን የካፒታል ገበያ ለመደገፍ የአይ-ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት ከኬንያው ናይሮቢ ሰኪውሪቲስ ኤክስቼንጅ ጋር አብሮ መስራት መጀመሩን አስታወቀ።

የአይ-ካፒታል ኢንስቲትዩት አፍሪካ መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ገመቹ ዋቅቶላ፣ እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ አዲስ የተጀመረው ካፒታል ገበያ ውጤታማ መሆን የሚችለው በአገሪቱ ያለው የሰው ኃይልና የተቋማቱ አቅም ሲጎለብት ነው።

ዘርፉ እንዲጎለብትና ውጤታማ እንዲሆን በዘርፉ ያሉት ባለሙያዎችን ማብቃት አስፈላጊ በመሆኑ ሥራውን ከአጋር አካላት ጋር በመሆን ለመሥራት የአይ-ካፒታል ኢንስቲቱዩት አፍሪካ ልምዱ ካለው የኬንያው ናይሮቢ ሴኪውሪቲስ ኤክስቼንጅና ከእንግሊዙ ቻርተርድ ባንከር ጋር በቁርኝት ለመሥራት ተፈራርሞ ሥራ መጀመሩን ተናግረዋል።

አይ-ካፒታል ከናይሮቢው ሴኩሪቲስ ኤክስቼንጅ ጋር ቁርኝት ፈጥሮ መሥራቱ በኢትዮጵያም የካፒታል ገበያ ውስጥ የተሰማሩና የሚሰማሩ ድርጅቶችንና የተቋማትን የሰው ሀብት ልማትንና ሌሎችንም ለመደገፍ ያስችላልም ብለዋል።

በ2015 ዓ.ም የተመሠረተው የአይ-ካፒታል ኢንስቲትዩት አፍሪካ ለባንኮች፣ ለኢንሹራንስ ኩባንያዎችና ለሌሎችም የመንግሥትና የግል ተቋማት የምክርና ስልጠና አገልግሎትንና የአቅም ማጎልበቻዎችን እየሰጠ ሲሆን በቀጣይም ይህንኑ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል አቶ ገመቹ።

የአይ-ካፒታል ኢንስቲትዩት አፍሪካ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ እንዲመሰረት ሠርቷል ያሉት ሥራ አስኪያጁ፣ የፋይናንሻል ዘርፉ ለዓለም አቀፍ ኢንቨስትመንት ሥራ ክፍት እንዲሆን ለማድረግ የሚኖረው ጥቅም ተጠንቶ መመስረቱንም አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ በደንብ ከዳበረ የአገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ሊያበረታታ እንደሚችል ሥራ አስኪያጁ ጠቁመው፣ ካፒታልን በሚያስፈልጉ ቦታዎች በመመደብ የአገሪቱን ልማት በከፍተኛ ደረጃ ያሳልጣል ብለዋል።

አቶ ገመቹ አክለውም፣ አደጋን የመጋራት መሠረትም በማመቻቸት ከባድ የሆኑ ነገር ግን ከፍተኛ ትርፍ የሚኖራቸው ፕሮጀክቶችን የፋይናንስ ችግር ይፈታል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እያደገ ሲሄድና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ትልልቅና ውስብስብ እየሆኑ ሲመጡ የካፒታል ገበያ መኖር ለአገሪቱ ይበልጥ አስፈላጊ እንደሚሆንም ተናግረዋል።

# 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በክልሎች ተከበረ

**በጋዜጣው ሪፖርተሮች**



አዲስ አበባ፡- 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን «ሰንደቅ ዓላማችን የብዝሐነታችን መገለጫ፤ የሉዓላዊነታችን ምሰሶ ነው» በሚል መሪ ቃል በክልሎች በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን በአዲስ አበባ ጨፌ ኦሮሚያ ጽ/ቤት በተከበረበት ወቅት የጨፌ ኦሮሚያ ምክትል አፈ ጉባኤ አቶ ኤሊያስ ኡመታ እንደገለፁት፣ አባቶቻችን ጠብቀው ያስተላለፉልንን የአገራችንን ሰንደቅ ዓላማ ክብር የአሁኑ ትውልድ አገሪቱን ከድህነትና ከጥገኝነት በማላቀቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ክብር ያላት አገር መገንባት ይጠበቅበታል።

ለሰንደቅ ዓላማ የምንሰጠው ፍቅርና ክብር እናትና አባቶቻችን በክብርና በጀግንነት ያቆዩልን በመሆኑ ለቀጣዩ ትውልድ በክብር የምናወርሰው የብዝሃነታችንና የአንድነታችን መገለጫ ታላቅ አገራዊ ዕሴት ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አሁን ካለው ክብር የበለጠ እንዲጎላ ከተፈለገ የአገሪቱን ሉዓላዊነት ይበልጥ በማስከበርና ከድህነት በፍጥነት በማላቀቅ መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

በመሆኑም በአገር አቀፍ ደረጃ በልማት፣ በኢኮኖሚ እንዲሁም በልዩ ልዩ ዘርፎች የተጀመረውን የለውጥ እንቅስቃሴ በቁርጠኝነት ከፍፃሜ በማድረስ መሆን እንደሚገባው ገልጸዋል።

በዓሉ በዚህ ወቅት መከበሩ አገሪቱ ሦስተኛውን ዙር የዓባይ ግድብ ሙሊት ባጠናቀቀችበት ወቅት መሆኑ፣ በአንድነት ለአገር ሉዓላዊነት መከበር ዜጎች በአንድነት በተነሱበት ወቅት መሆኑ እንዲሁም ለአገር አንድነትና ምሰሶ የሆነውን የብሔራዊ መግባባት መርሃ ግብር በጀመርንበት ማግስት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል ብለዋል።

ይህን የሰንደቅ ዓላማ ቀን ስናከብር ለተጀመረው አገራዊ ምክክር ለማሳካት ሁላችንም የድርሻችንን መወጣት አለብን ብለዋል።

15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በሶማሌ ክልል ርዕሰ ከተማ በጅግጅጋ ሲከበር ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ ሙሐመድን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግሥት ሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

በዓሉ በጅግጅጋ ከተማ በሚገኘው በቀርያን ዶዳን አዳራሽ የተከበረ ሲሆን፣ በሌሎች የክልሉ ከተሞችም በድምቀት ተከብሯል።

በተመሳሳይ 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በባሕር ዳር ከተማም በድምቀት ተከብሯል።

የአማራ ክልል ምክር ቤት ምክትል አፈጉባዔ አማረ ሰጤ በዚሁ ወቅት፣ ሰንደቅ ዓላማ የአገር ክብርና ሉዓላዊነት መገለጫ፣ የጀግንነታችንና የአኩሪ ታሪካችን ማሳያ መሆኑን ገልፀዋል።

ለሰንደቅ ዓላማችን ክብር ብዙ ጀግኖች ተዋድቀዋል ያሉት አቶ አማረ፤ አሁንም አሸባሪውን የሕወሓት ኃይል በመፋለም የአገርን ህልውና ለማረጋገጥና ሰንደቅን ከፍ ለማድረግ በግንባር መከላከያ ሠራዊቱና ጥምር ጦሩ እየተፋለመ ነው ብለዋል። ሕዝቡ ለሰንደቅ ዓላማ ብሎም ለአገር ያለውን ፍቅር ሠራዊቱን በመደገፍ ሊገልፅ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ 15ኛው የሰንደቅዓላማ ቀን በሲዳማ ክልል በሀዋሳ ከተማ ሲከበር በመርሃ ግብሩ ላይ ተገኝተው መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ሰንደቅ ዓላማችን የአገራችን ክብርና የሉአላዊነት መገለጫ ነው ብለዋል። ለሰንደቅ ዓላማ ክብር የደም ዋጋ የከፈሉ ሁሉ ክብር ይገባቸዋልም ብለዋል።

የሰንደቅ ዓላማን ታሪክ ለትውልድ በአግባቡ ማስተማር ይገባል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የሰንደቅ ዓላማ ቀን መከበሩም ለሕብረ-ብሔራዊ አንድነታችን መጠናከር፣ ለሉዓላዊነታችን መከበር እንዲሁም ይበልጥ ብሔራዊ መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም የሚኖረው ሲሆን ለአገር ክብርና ጥቅም ሁላችንም እንደ ዜጋ የበኩላችንን እንድንወጣ አደራ ጭምር በማለት መልዕክታቸው አስተላልፈዋል።

የሰንደቅ ዓላማ ቀን በጋምቤላ ክልልም ተከብሯል። የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኡሞድ ኡጁሉ በበዓሉ አከባበር ላይ ተገኝተው እንዳሉት፤ በዓሉ ለአገር ክብርና ጥቅም ሁላችንም እንደዜጋ የበኩላችንን ለመወጣት በሰንደቅ ዓላማ ፊት ዳግም ቃላችንን የምናድስበት ነው።

በዚህ ወቅት የሰንደቅ ዓላማ ቀን መከበሩ ለሕብረ ብሔራዊ አንድነታችን መጠናከር፣ ለሉዓላዊነታችን መከበርና ይበልጥ ብሔራዊ መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም አለው ብለዋል።

በሌላ በኩልም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን በክልሉ ቦንጋ ከተማ ተከብሯል።

የርዕስ መስተዳድሩ ማህበራዊ ጉዳይ አማካሪ አቶ ደነቀ ማሞ፣ ሰንደቅ ዓላማ የአንድ አገር መለያና መገለጫ እንዲሁም ለእኛ ለኢትዮጵያን ግን የአንድነታችንና የሉዓላዊነት ዓርማ በመሆኑ ልዩ ያደርጋል ብለዋል።

ሰንደቅ ዓላማ በኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት፣ መዋደድና መፈቃቀር የተመሠረተ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ በአንድነት መቆም ይገባል ብለዋል።

በተመሳሳይ የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን በሐረሪ ክልል ተከብሯል። በዓሉ በክልሉ ምክር ቤት አዳራሽ ፊት ለፊትና በሁሉም ተቋማት ሰንደቅ ዓላማ በመስቀልና በሰንደቅ ዓላማ ፊት ቃለ መሀላ በመፈፀም ተከብሯል።

የሐረሪ ክልል ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ አቶ አሪፍ መሃመድ በሥነ ሥርዓቱ ወቅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮው ሰንደቅ ዓላማ ቀን የውስጥ ቅጥረኛ ተላላኪዎችና በቅርብም ከሩቅም ያሉ የውጭ ጠላቶች አቅደውና ተናብበው ብሔራዊ አንድነታችንንና ሉዓላዊነታችንን አደጋ ላይ ለመጣል እየሠሩ ባሉበት ወቅት መከበሩ ለኅብረ-ብሔራዊ አንድነት መጠናከር ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

በዓሉ በዚህ ወቅት መከበሩም ለሕብረብሔራዊ አንድነታችን መጠናከር፣ ለሉዓላዊነታችን መከበርና ይበልጥ ብሔራዊ መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም እንዳለው ተናግረዋል።

# «በደማችን ያስከበርናትን ሰንደቅ ዓላማ በላባችን ከፍ እናደርጋታለን»

*- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

አዲስ አበባ፡- በደማችን ያስከበርናትን ሰንደቅ ዓላማ በላባችን ከፍ እናደርጋታለን ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ፡፡ ሰንደቅ ዓላማችን የትናንት የጋራ ታሪካችንን፤ የዛሬ ጥረታችንን እና የነገ ተስፋችንን እንዲሁም ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጣምሮ የያዘ የክብራችን እና የማንነታችን ማኅተም መሆኑንም ባወጣው መግለጫ አትቷል፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት 15ኛውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን በማስመልከት ትናንት በሰጠው መግለጫ እንዳመለከተው፤ 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ስናከብር በደም ጠብቀን ያቆያናትን ሀገራችንን በደማችን እና በላባችን እያጸናን ነው፡፡ ሰንደቅ ዓላማ የሀገር ምልክት ነው። ይሄንን ዓርማ ይዘው ጀግኖች መሥዋዕትነት ከፍለዋል። በዓለም አደባባይ አሸንፈዋል። ይህ ሰንደቅ ዓላማ ከልጅ እስከ ዐዋቂ ልብ ውስጥ የማይፋቅ ማኅተም አሳርፏል።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የትናንት የጋራ ታሪካችንን፤ የዛሬ ጥረታችንን እና የነገ ተስፋችንን እንዲሁም ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጣምሮ የያዘ የክብራችን እና የማንነታችን ማኅተም ነው ያለው መግለጫው፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዘመናት ሂደት ሰንደቅ ዓላማዋን አንግበው ለሉዓላዊነቷ እና ለአንድነቷ የተዋደቁ የጀግኖች ልጆች እናት ናት፡፡ አሁን ባለንበት ዘመንም ቢሆን ሰንደቅ ዓላማዋን አንግቦ፣ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ የተነሡ ጠላቶቿን አሳፍሮ የሚመልስ ትውልድ ያላት፣ የእልፍ ጥቁር አንበሶች ምድር ናት፡፡ የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶቻችን ከሀገር ውስጥ ባንዳ አሸባሪዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል፡፡ ሆኖም በልጆቿ ደምና ብርታት ምኞታቸው ቅዠት ሆኖ ቀርቷል ሲል ገልጿል፡፡

መግለጫው እንዳለው፤እኛ ካልመራናት ትፍረስ ብለው፣ በየአካባቢው ግጭት ጠንስሰው፣ ጠብን ስፖንሰር አድርገው ሕዝባችንን ተስፋ ለማስቆረጥ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ እያንዳንዱ የሀገር ብተና ሤራቸው ተራ በተራ ሲከሽፍባቸው ደግሞ ሀገር ጠባቂ መከላከያ ሠራዊታችንን በሌሊት አጥቅተው ጦርነት ከፍተውብናል፡፡ ይህ ሁሉ ወጥመድ ግን ለሰንደቃቸው ክብር በሚሠዉ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች የጋራ ርብርብ ከግቡ ሳይደርስ መክኖ ቀርቷል፡፡

በተለይም የሀገር መከላከያ ሠራዊታችን እና የክልል የጸጥታ ኃይሎች በሀገራችን ላይ ጦርነት የከፈቱ አሸባሪዎችን ድል ነሥተው፤ ሀገራቸውን ከመፍረስ መታደጋቸውና በደማቸው ሰንደቅ ዓላማችንን ማስከበራቸውን መግለጫው አመልክቶ፤ ጠላቶቻችን ጦርነት የከፈቱብን ሁሉንም ትኩረታችንን ወደ ጦር ግንባር አድርገን በሌሎች ዘርፎች ሽባ እንድንሆን አስበው ነበር፡፡ ዓላማቸው ኢትዮጵያን አዳክሞ ማፍረስ ነበር፡፡ ነገርግን ይህ ዓላማቸው በቁርጥ ቀን ልጆቿ ብርታትና እና በሕዝባችን ድጋፍ ሳይሳካ መቅረቱን አስታውቋል፡፡

"በደማችን እየጠበቅን በላባችን እናጸናለን"በሚል ዕሳቤ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ከጫፍ እስከ ጫፍ በአንድ እጃቸውእያረሱ፤ በሌላኛው እጃቸው እየተኮሱ ሀገራቸውን እየገነቡ ነው። በአንድ በኩል ከጠላት እየተከላከሉ፣ በሌላ በኩል የሰብል ምርታቸውን በብዙ እጥፍ አሳድገዋል የሚለው መግለጫው፤ በዚህ ሂደትም ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ የግብርና ምርቶችን በማምረት፤ እንደ ሕዳሴ ግድብ ያሉ የተጀመሩ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ወደላቀ ምዕራፍ በማድረስ እና ሌሎቹንም በማጠናቀቅ ሕዝባችንን ተስፋ ሊያስቆርጡ የተነሡ ጠላቶቿን ተስፋ አስቆርጣለች፡፡ በዚህም የሀገር ክብርና ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ እንዲል ተደርጓል ሲል መግለጫው አብራርቷል፡፡

እንደ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የልማት ሥራዎችን እያጧጧፉ ጎን ለጎን የተከፈተባቸውን ጦርነት ሲመክቱ፤ ዐዋቂ እና ወጣት አትሌቶቻችን ደግሞ በዓለም አደባባይ በሀገር ፍቅር ስሜት ተናበው የሀገራቸውን አሸናፊነት ለወዳጅም ለጠላትም ዐውጀዋል፡፡ ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገው አውለብልበዋል፡፡ ከሀገር አልፈው የአፍሪካ ኩራት ሆነዋል፡፡

ኢትዮጵያችን በብዙ ፈተና በተወጠረችበት በዚህ ወቅት ጠላቶቿን እየመከተች የልማት ሥራዎችን በታላቅ ስኬት መቀጠሏን ያስታወቀው መግለጫው፡፡ የምግብ ሉዓላዊነት ሳይኖር የሀገር ሉዓላዊነትን ማስከበር ከባድ ነው። በልመና ስንዴ የሰንደቅ ዓላማ ክብርን በዘላቂነት ማረጋገጥ አዳጋች ነው። ጀግኖቻችን በጦር ግንባር በደም ያስከበሯትን ሰንደቅ ዓላማ፤ በልማት ትግል በላባችን ከፍ ለማድረግ፣ ሁላችንም በተሠማራበት መስክ የበኩላችንን ሚና መወጣት ይኖርብናል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመግለጫው አሳስቧል፡፡

# የዓባይ ግድብ የነገዋን ኢትዮጵያ ዛሬ ለመገንባት መሠረት የሚጥል መሆኑን የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች ገለጹ

- ግድቡን ለፍጻሜ ለማብቃት በትብብር ይሠራሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ የነገዋን ኢትዮጵያ ዛሬ ለመገንባት መሠረት የሚጥል መሆኑን የተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ገለጹ፡፡ አመራሮቹ የፖለቲካ ልዩነት ሳይገድባቸው ግድቡን ለፍጻሜ ለማብቃት በትብብር እንደሚሠሩም አረጋግጠዋል፡፡

ከ50 በላይ ከሚሆኑ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ አመራሮች የዓባይ ግድብን የግንባታ ሂደትና አሁናዊ ገጽታ በጎበኙበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ግድቡ የአንድነታችን ማሰሪያ በመሆኑ የፖለቲካ ልዩነት ሳይገድበን ለፍጻሜ ለማብቃት በትብብር እንሠራለን ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ ዓለሙ ፣ የኢዜማ ዋና ጸሐፊ አቶ አበበ አካሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ዘሪሁን ገብረእግዚአብሔር በፖለቲካው ዘርፍ ያላቸውን ልዩነት በሰለጠነ መንገድ እየፈቱ የኢትዮጵያን ከፍታ በሚያረጋግጡ እንደ ዓባይ ግድብ ባሉ የጋራ ልማቶች ላይ በትብብር መሥራት ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

«ግድቡ ከፖለቲካ በላይ የሆነ የአገር ሀብት ነው» ያሉት አመራሮቹ የነገዋን ኢትዮጵያ ዛሬ ለመገንባት መሠረት የሚጥል ነው ብለዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ ለአገር አንድነት፣ ለሰላም መስፈንና ለልማት መረጋገጥ የበኩላቸውን እንደሚወጡም ቃል ገብተዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ለግድቡ ግንባታ ስኬት እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አድንቀው በመንግሥት በኩል የታየው ቁርጠኝነትም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያውያን አሻራ ያረፈበትን የዓባይ ግድብ የመጎብኘት ዕድል በማግኘታቸው መደሰታቸውንም ገልጸዋል።

ልዩነቶችን ወደ ጎን ትቶ ብሔራዊ ምልክት በሆኑ ጉዳዮችና በአገር ልማት ላይ ማተኮር ከኢትዮጵያ አልፎ ቀጣናዊ ትስስርን ለመፍጠርም አስተዋጽኦው የጎላ እንደሆነ ተናግረዋል።

«የዓባይ ግድብ የትውልድ ቅርስ ነው» ያሉት የፖለቲካ አመራሮቹ ግድቡ የገዢው ፓርቲ ወይም የመንግሥት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም በመሆኑ ግንባታውን በጋራ ማሳካት አለብን ብለዋል።

ከዓባይ ግድብ ባሻገር በሌሎች አገራዊ ፕሮጀክቶች ላይም የራሳቸውን አሻራ ለማሳረፍ ቁርጠኛ መሆናቸውን አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ እያዋጣ ዛሬ ላይ ያደረሰው ግድብ ኃይል አመንጭቶ ለፍሬ መብቃቱን በአካል ተገኝተው ማረጋገጣቸው እንዳስደሰታቸውም ገልጸዋል።

ግድቡ ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ድረስም የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለመደ ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በጉብኝቱ ከ50 በላይ ከሚሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች የተውጣጡ አመራሮች ተሳትፈዋል።

# የተጋረጠብንን አደጋ በመመከት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ በመሆን ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገን የምንሰቅል ኩሩ፣ ለአንድነት የቆምንና ለጠላት የማንበገር ኢትዮጵያውያን መሆናችንን ማሳየት ይገባናል ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የሚከበረው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ከቅርብም ከውጭም ያሉ ጠላቶች የውስጥ ቅጥረኞችንና ተላላኪዎቻቸውን ይዘው፣ አቅደውና ተናበው ብሔራዊ አንድነታችንን እና ሉአላዊነታችንን አደጋ ላይ ለመጣል እየሠሩ ባሉበት ወቅት መከበሩን ገልፀው፤ ይህ መሆኑ ለሕብረ ብሔራዊ አንድነታችን መጠናከር፣ ለሉአላዊነታችን መከበር እና ይበልጥ ብሔራዊ መነቃቃትን ለመፍጠር ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል ብለዋል፡፡

በዓሉ ለአገር ክብርና ጥቅም ሁላችንም እንደዜጋ የበኩላችንን ለመወጣት በሰንደቅ ዓላማ ፊት ዳግም ቃላችንን የምናድስበት ዕለት ይሆናልም ሲሉ አክለዋል፡፡

ዜጎች ለአገራቸው ያላቸውን ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት ለሰንደቅ ዓላማ በሚሰጡት ስሜት ይገለፃል ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ በተለይም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰንደቅ ዓላማ ትልቅ ሥፍራ ያለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ለሰንደቅ ዓላማ የምናሳየው ክብርና ፍቅር ከእናት አባቶቻችን በክብር ወርሰነው እና በክብር ለቀጣዩ ትውልድ የምናስተላልፈው ነው ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰንደቅ ዓላማ  የሚሰጠው ክብር በሕዝቡ ልብ ውስጥ ታትሞ የሚቆይ የብዝኃነት፣ የአንድነት እና የሉአላዊነት መገለጫ ታላቅ አገራዊ ዕሴት ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ሰንደቅ ዓላማ የመስዋዕትነት፣ የሉአላዊነት፣ የግዛት አንድነት እና የአብሮነት አርማ ምልክት በመሆኑ ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ለሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠት፣ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት ሲሉም አክለዋል፡፡

ሰንደቅ ዓላማችን የሕዝባችን የደም ውጤት ነው ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ዛሬም ለሰንደቅ ዓላማ ዋጋ የሚከፍለውና የአገር መከታ ለሆነው ሠራዊት ክብር ምሥጋና እንደሚገባው ገልፀዋል፡፡

የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን በዓል በተለያየ መልኩ እየተከበረ 14 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በያዝነው ዓመትም «ሰንደቅ ዓላማችን የብዝኃነታችን መገለጫ የሉአላዊነታችን ምሰሶ ነው» በሚል መሪ ሃሳብ አገራዊና ወቅታዊ ሁኔታውን በዋጀ መልኩ ለ15ኛ ጊዜ በትናንትናው ዕለት በአገር አቀፍ ደረጃ ተከብሮ ውሏል፡፡

የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 63/2006 በተሻሻለው አንቀፅ ሁለት መሠረት በየዓመቱ ጥቅምት ወር በገባ በመጀመሪያው ሳምንት ሰኞ እንደሚከበር ተደንግጓል፡፡

# መንግሥት በትግራይ ክልል የሚገኙ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስዳቸው ርምጃዎች የግድ አስፈላጊ የሆኑት በአሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ ጥቃት የተነሣ ብቻ ሳይሆን ከአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅቶ በሚፈጽማቸው ተግባራት ምክንያት ጭምር ነው ያለው መግለጫው፤ የአገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር የኢትዮጵያ መንግሥት የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የፌዴራል ተቋማትንና ታላላቅ መሠረተ ልማቶችን የግድ መጠበቅ አለበት ብሏል።

መንግሥት የአገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በተለይም የአየር ክልልን በሚገባ ከማስከበር አንጻር መጠበቅ የግድ መሆኑን ገልጿል።

በአሁኑ ወቅት በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ግጭት፤ አሸባሪው ሕወሓት ነሐሴ 18 ቀን 2014 በሙሉ ዐቅሙ የከፈተውን ጥቃት ተከትሎ የመጣ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው ያለው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ፤ ይህም የኢትዮጵያ መንግሥት በሚያዝያ ወር ያወጀውን በሰብአዊነት ላይ የተመሠረተ የተኩስ አቁም የጣሰ ነው ብሏል። የመንግሥት ጥረት ምንም ዋጋ ስላልተሰጠው፣ አሸባሪው ሕወሓት በሁለት ዓመት ውስጥ አገሪቱን ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ግጭት አስገብቷታል ሲል አብራርቷል።

አሸባሪው ሕወሓት ሦስተኛውን ግጭት የከፈተው በአፍሪካ ኅብረት በኩል በሚደረገው የሰላም ንግግር፣ ያለ ቅድመ ሁኔታ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ላይ ለመነጋገር የኢትዮጵያ መንግሥት ዝግጁነቱን ከገለጸ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ መሆኑን አስታውሶ፤ ቡድኑ ለተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት በበተነው ደብዳቤና ለልዩ መልዕክተኞችና መቀመጫቸውን በአዲስ አበባ ላደረጉ ዲፕሎማቶች ጥቃት የመክፈት ፍላጎቱን በግልጽ ማመልከቱን ጠቅሷል።

በመሆኑም አሁን ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂው አሸባሪው ሕወሓት መሆኑ የተረጋገጠ ነው። አሁንም ጊዜና ቦታ ከተሰጠውም ሌላ ዙር ግጭት እንደሚፈጥር ከሰሞኑ መግለጫዎቹ ለመረዳት ይቻላል ብሏል አገልግሎቱ በመግለጫው፡፡

አሸባሪው ሕወሓት በሙሉ ዐቅሙ ጥቃት ከመክፈቱ በፊት የኢትዮጵያን የአየር ክልል ደጋፊዎቹ በሆኑ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ሲያስደፍር ቆይቷል። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስዳቸው ርምጃዎች የግድ አስፈላጊ የሆኑት በአሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ ጥቃት የተነሣ ብቻ ሳይሆን ከአገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅቶ በሚፈጽማቸው ተግባራት ምክንያት ጭምር መሆኑን መግለጫው በማመልከትም፤ የአገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር የኢትዮጵያ መንግሥት የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የፌዴራል ተቋማትንና ታላላቅ መሠረተ ልማቶችን የግድ መጠበቅ አለበት ብሏል።

መግለጫው እንዳለው፤ እነዚህ ተግባራት መፈጸሙ መንግሥት ሰብአዊ እርዳታን ለተረጂዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲያሳልጥ የሚረዳው ይሆናል። በአንድ በኩል እነዚህን ዓላማዎች እያስፈጸመ በሌላ በኩል ደግሞ በአፍሪካ ኅብረት አማካኝነት ለሚካሄደው የሰላም ውይይት ዝግጁ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግሥት በድጋሚ ያረጋግጣል። ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ሁለንተናዊና በንግግር ላይ የተመሠረተ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን መንግሥት ያምናል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አግባብነት ባላቸው አሠራሮችና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ ሕጎች በጽኑ የሚገዛ መሆኑን መንግሥት ግልጽ ለማድረግ ይፈልጋል ያለው መግለጫው፤ ንጹሐን እንዳይጎዱ ለመከላከል እንዲቻል የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ጦርነቱ በከተሞች ውስጥ እንዳይደረግ ጥንቃቄ እያደረገ ይገኛል። ይሄንን በጽኑ ለመፈጸም እንዲቻልም ለሁሉም ተዋጊ አሐዶች ጥብቅ መመሪያ መተላለፉን መግለጫው አመልክቷል።

በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በሆኑ አካባቢዎችም ሰብአዊ እርዳታ በተሻለ መንገድ መቅረብ እንዲችልና የእርዳታ ሠራተኞች ደኅንነት የተጠበቀ እንዲሆን መንግሥት ከእርዳታ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን አመልክቶ፤ አሸባሪው ሕወሓት ንጹሐንን እንደ ጦር መከላከያ የመጠቀምና ሲቪል ተቋማትን ለወታደራዊ ሠፈርነት የመጠቀም የቆየ ልማድ ስላለው ሕዝቡና የእርዳታ ሠራተኞች ራሳቸውን ከአሸባሪው ሕወሓት ወታደራዊ ተቋማት እንዲያርቁ የኢትዮጵያ መንግሥት ጥሪ ማድረጉን ገልጿል።

በትግራይ ክልል የሚገኙ ዜጎቹን ደኅንነት ለመጠበቅ በሕግ የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን ለመወጣት የኢትዮጵያ መንግሥት ያለውን ዝግጁነት በዚሁ አጋጣሚ ያረጋግጣል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በመግለጫው አስታውቋል።



# ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ችላ ምርቶቿን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

«አካባቢዎቹ ያስገኙት ምርት በእጅጉ አበረታች ነው። በስንዴ አምራችነት ያገኘነውን አስደሳች ውጤት በሌሎች ምርቶችም እንደሚቀጥል ያመላክታል» ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

አገራችን የምግብ ዋስትናዋን አረጋግጣ በዓለም ገበያ በምርቶቿ መሳተፏ የሩቅ ጊዜ ህልም ሳይሆን፣ እየቀረበ የሚገኝ የጥረት ውጤት መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በጉብኝቱ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንንን ጨምሮ የፌዴራል እና የክልል ከፍተኛ አመራሮች ተሳትፈዋል፡፡

# «ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችንን የመዋደድና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሰንደቅ ዓላማ አንድ አገር ነፃነቱን፣ ሉአላዊነቱን፣ የሚያሳይበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ ዜጎች ለአገራቸው ያላቸውን ፍቅርና ክብር የሚገልጹበት ዋናው ብሔራዊ አርማና ምልክት ነው።  በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ ለሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠትና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።  «ለእኛ ኢትዮጵያውያን ሰንደቅ ዓላማ  የነፃነት፣ የአርበኝነት፣ የአይበገሬነትና የታሪካችን አርማ ነው»።  የአንድ አገር ሕዝብ ለጋራ ዓላማ የሚያሰባስብና የሚያነሳሳ ነው። በመሆኑም አንድ አገር የሚለይበት የሚታወቅበት አንድ ሰንደቅ ዓላማ ብቻ ነው ብለዋል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ «በአገራችን እንዳየነው በየጊዜው ሥርዓቶች አንዳንድ ጊዜም ደም ባፋሰሰ ሁኔታ ሲለዋወጡ በሰንደቅ አላማው መሃል ያለው አርማ እንጂ የሰንደቅ ዓላማው ቀለም አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀዩ አልተነካም። ሰንደቅ ዓላማ የአገር መለያ እንደመሆኑ መጠን በነጋ በጠባ፤ ሥርዓት በተለዋወጠ ቁጥር የሚለወጥ አይደለም ነው ያሉት።

ፕሬዚዳንቷ፤ አገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ፈተናዎችን አስተናግዳለች።  ይህ ትውልድ ከዚህ ለማምለጥ ባለመቻሉ ብዙ ዜጎቻችንን አጥተናል፤ ብዙዎች ቆስለዋል፤ ተፈናቅለዋል። የጦርነት አውዳሚነት፣ ጎጂነት፣ እያየነው፣ እየኖርነው ነው።  እንደ አገር ችግራችን የምንፈታው የአገራችን መለያ የሉአላዊነት መገለጫ በሆነው ሰንደቅ ዓላማችን ጥላ ስር ስንሰባሰብ መሆኑን ገልጸዋል።

ሰንደቅ ዓላማችን በጉልህ የሚታወቀው በአርበኝነት፣ በመስዋዕትነትና አገርን ለጠላት አላስነካም በማለት መሆኑን የጠቆሙት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ የብዝሃነት፣ አብሮ የመኖር፣ የመደማመጥ፣ የመወያየት፣ እርስ በእርሱ የመመካከር፣ በማንኛውም ሁኔታ ከራስ በላይ አገርን የማስቀደም ምልክት ነው።

ሰንደቅ ዓላማችንን የመዋደድ፣ የመተሳሰብ አርማ ልናደርገው ይገባል።  ውይይትን ንግግርን፣ ልዩነትን ማስተናገድና ሰንደቅ ዓላማችን እስከዛሬ ድረስ እንዳስከበረን ሁሉ ነገም እንደትናንቱ የምንመካበት፣ የምንከባበርበት፣ በከፍታ ላይ የምናሳየው መሆን እንዳለበት ፕሬዚዳንቷ አሳስበዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው፤ 15ኛው የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ቀን ልዩ የሚያደርገው ከውስጥም ከውጭም የሚፈታተኑ ኃይሎችን ለመመከት ከፍተኛ መስዋዕነት በመክፈል የአገራችን ሉአላዊነት ለማስከበር ከፍተኛ ትግል በምናደርግበት  ወቅት የሚከናወን መሆኑ  ነው። የአገራችን ታሪክ ሕዝባችን በከፍተኛ መስዋዕትነት ለዘመናት የአገራችን ህልውና ሲያስከብር ኑሯል፤ አሁንም እያስከበረ ይገኛል።

አቶ ታገሰ እንደገለጹት፤ የሰንደቅ ዓላማ ቀንን በልዩ ሁኔታ ስናከብር ያስመዘገብናቸውን ድሎች አጥብቅን በመያዝ፤ አሁንም ያሉብን ፈተናዎች  በጋራ በመቆም በጽናት በመታገል ኢትዮጵያዊነት አብቦና ለምልሞ ሁላችንም አገራችን ወደ ከፍታ ለማሸጋገር የሚያስችል ወቅት ስለሆነ ነው።

የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ በሰንደቅ አላማ ቀን ላይ ተገኝተው የሁለቱም ምክር ቤት አመራሮችና ሠራተኞች የሕዝቦችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመንግሥት የተነደፉ እቅዶች ውጤታማ እንዲሆኑ ቃለመሃላ አስፈጽመዋል።

የዘንድሮ የሰንደቅ ዓላማ ቀን የሁለቱ ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንትና ተወካዮች፣ የመከላከያ ሰራዊት አባላትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መኖር ታሪክን ሕያው ማድረግ ነው!

አገራችን ኢትዮጵያ በየዘመኑ ስለአገራቸው ሰንደቅ ዓላማ ክብር ህይወታቸውን ሳይሰስቱ የገበሩ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጀግኖችን ያፈራች አገር ነች። ከዚህም የተነሳ እንደ አገር የነጻነትና የአትንኩኝ ባይነት ተምሳሌት በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጠቃሽ ናት።

ይህ የህዝባችን ለሰንደቅ ዓላማ ያለው ክብር በየዘመኑ በምድሪቱ በበቀሉ ባንዳዎች በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ለማለፍ የተገደደባቸው አጋጣሚዎች ቢበዙም፤ አገር እንደ አገር ችግር ሲያጋጥማት ግን ከተግዳሮቶች በላይ ሆኖ በመግዘፍ አገርን ሲታደግ መመልከት የተለመደ ነው።

አገር በብዙ መስዋዕት ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግራ እንደመጣች ከራሱ ተጨባጭ የመስዋእትነት ታሪክ እየተማረ የመጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለአገርና ለሰንደቅ ዓላማ ለሚከፈል መስዋዕትነት ከፍ ያለ ከበሬታ ያለው፤ ከዚህ በመነጨም ለአገር ለመሞት ሁሌም ዝግጁ ነው። ይህ ደግሞ ዓለም አቀፍ ምስክርነት የሚቸረው ብሄራዊ እሴታችን ጭምር ነው።

ሕዝባችን የአገርህ ሉአላዊነት አደጋ ውስጥ ወደቀ፤ ሰንደቅ ዓላማህ ተደፈረች ሲባል፤ ልዩነቶቹን ሁሉ ወደ ጎን በመተው ቀፎው እንደተነካበት ንብ የመትመሙ እውነታ የታሪኩ ሰፊ አካል ነው፤ ስለሰንደቅ ዓላማህ የሚከፈል መስዋዕትነት ትውልድ ተሻጋሪ ስለመሆኑ ከተጋድሎ ታሪኩ የተረዳ ነው።

በዛሬው ትውልድ መካከል እንደቀደመው ዘመን ለሰንደቅ ዓላማ ደንታቢስ የሆኑ ባዳዎች ቢኖሩም፤ አብዛኛው የትውልዱ አካል ግን ሰለ ሰንደቅ ዓላማህ መሞት የክብር ሞት መሆኑን የተረዳና ለዚህም ራሱን ያዘጋጀ ስለመሆኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት እየተስተዋለ ያለው እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ዛሬም ቢሆን ሰንደቅ ዓላማዋን አንግበው፣ አገርን ከመፍረስ፤ ሕዝብን ከውርደት ለመታደግ ሕይወታቸውን መስዋዕት አድርገው የሰጡ፤ የሚሰጡና ለመስጠትም ዝግጁ የሆኑ ጀግኖች እልፍ ናቸው። በዚህም አይነሱም ስንባል ተነስተን መራመድ፤ አበቃላቸው ስንባል በአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጅማሬ ውስጥ በመገኘት ለጠላቶቻችንም ለወዳጆቻችንም እንቆቅልሽ እንደሆንን ቀጥለናል።

በቅርቡ እንኳን የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶቻችን /ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ/ ከአገር ውስጥ ባንዳዎች ጋር ተባብረው አገሪቱን እንደአገር ለመበተን የሄዱበት የሴራ መንገድ ከህልምነት ወደ ቅዠትነት የተለወጠው በነዚሁ ለአገር ክብር ጨርቄን ማቄን በማይሉ፤ ለሰንደቅ ዓላማና ለአገር መሞት ክብር መሆንን በትውልዶች መንሰላሰል ውስጥ መረዳት በቻሉ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ነው።

ሰንደቅ ዓላማ ለነዚህ ጀግኖች ከክብር ሁሉ ከፍ የሚለው የክብራቸው መገለጫ ነው። ከዚህ ክብራቸው በላይ ዋጋ ሊሰጡት ሆነ ሊደራደሩበት የሚችሉበት ሌላ ዋጋ ያለው ነገር የላቸውም። ሕይወትን ለባንዲራ ክብር ዋጋ አድርጎ መክፈል አገርና ሕዝብን መታደግ ከዚያም በላይ ታሪክን ሕያው አድርጎ የማስቀጠል ከፍ ያለ ተልዕኮ እንደሆነ የተረዱ ናቸው ።

በተለይም በአሁኑ ወቅት የተጀመረውን ለውጥ ለማስቀጠል የሚከፈል መስዋዕትነት የቱንም ያህል በታሪክ ውስጥ የክብር ስፍራ እንዳለው፤ ለውጡ ይዞት የመጣውን ተስፋና ተስፋው በጠላቶቻችን መንደር የፈጠረውን መደናገጥና ከዚህ መደናገጥ የተፈጠረውን ተግዳሮት ማሰብ ብቻ ተገቢ ነው።

ይህንን ተግዳሮት ሰብሮ በመውጣት የአገርን ህልውና ከስጋት ለመታደግ እልፍ አእላፍ ጀግኖች የከፈሉት መስዋዕትነት ዛሬ ላይ አገርን እንደ አገር ለማስቀጠል ከፈጠረው ማስተማመኛ ጎን ለጎን ስለ ሰንደቅ ዓላማ በዘመናት መካከል የከፈልነውን መስዋዕትነት በማደስ ትውልዱ የራሱ ታሪክ ባለቤት እንዲሆን ያስቻለ ነው። የዚህ የተጋድሎ ታሪክ አካል የሆኑ የቁርጥ ቀን ጀግኖቻችንም የነገው ታሪካችን ትልቁ አካል፤ አብሪ ከዋክብቶች ናቸው !


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## 15ኛውን የሰንደቅ ዓላማ ቀን እንዲሁም በሰሜን ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የመከላከል ርምጃ አስመልክቶ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሰጠው መግለጫ

### በደማችን ያስከበርናትን ሰንደቅ ዓላማ በላባችን ከፍ እናደርጋታለን!

15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ቀን ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ ተከብሮ ይውላል። ቀኑን ስናከብር በደም ጠብቀን ያቆያናትን አገራችንን በደማችን እና በላባችን እያጸናን ነው። ሰንደቅ ዓላማ የአገር ምልክት ነው። ይሄንን ዓርማ ይዘው ጀግኖች መሥዋዕትነት ከፍለዋል። በዓለም አደባባይ አሸንፈዋል። ይህ ሰንደቅ ዓላማ ከልጅ እስከ ዐዋቂ ልብ ውስጥ የማይፋቅ ማኅተም አሳርፏል።

የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የትናንት የጋራ ታሪካችንን፤ የዛሬ ጥረታችንን እና የነገ ተስፋችንን እንዲሁም ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አጣምሮ የያዘ የክብራችን እና የማንነታችን ማኅተም ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በዘመናት ሂደት ሰንደቅ ዓላማዋን አንግበው ለሉዓላዊነቷ እና ለአንድነቷ የተዋደቁ የጀግኖች ልጆች እናት ናት። አሁን ባለንበት ዘመንም ቢሆን ሰንደቅዓላማዋን አንግቦ፣ ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ የተነሡ ጠላቶቿን አሳፍሮ የሚመልስ ትውልድ ያላት፣ የእልፍ ጥቁር አንበሶች ምድር ናት። የቅርብ እና የሩቅ ጠላቶቻችን ከአገር ውስጥ ባንዳ አሸባሪዎች ጋር ተባብረው ኢትዮጵያን ለመበታተን መሄድ እስከሚችሉት ድረስ ተጉዘዋል። ሆኖም በልጆቿ ደምና ብርታት ምኞታቸው ቅዠት ሆኖ ቀርቷል።

እኛ ካልመራናት ትፍረስ ብለው፣ በየአካባቢው ግጭት ጠንስሰው፣ ጠብን ስፖንሰር አድርገው ሕዝባችንን ተስፋ ለማስቆረጥ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም።

እያንዳንዱ የአገር ብተና ሴራቸው ተራ በተራ ሲከሽፍባቸው ደግሞ አገር ጠባቂ መከላከያ ሠራዊታችንን በሌሊት አጥቅተው ጦርነት ከፍተውብናል። ይህ ሁሉ ወጥመድ ግን ለሰንደቃቸው ክብር በሚሠው ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች የጋራ ርብርብ ከግቡ ሳይደርስ መክኖ ቀርቷል።

በተለይም የአገር መከላከያ ሠራዊታችን እና የክልል የጸጥታ ኃይሎች በአገራችን ላይ ጦርነት የከፈቱ አሸባሪዎችን ድል ነሥተው፤ አገራቸውን ከመፍረስ ታድገዋል። በደማቸው ሰንደቅ ዓላማችንን አስከብረዋል።

ጠላቶቻችን ጦርነት የከፈቱብን ሁሉንም ትኩረታችንን ወደ ጦር ግንባር አድርገን በሌሎች ዘርፎች ሽባ እንድንሆን አስበው ነበር። ዓላማቸው ኢትዮጵያን አዳክሞ ማፍረስ ነበር። ነገር ግን ይህ ዓላማቸው በቁርጥ ቀን ልጆቿ ብርታትና እና በሕዝባችን ድጋፍ ሳይሳካ ቀርቷል።

"በደማችን እየጠበቅን በላባችን እናጸናለን"በሚል ዕሳቤ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ከጫፍ እስከጫፍ በአንድ እጃቸው እያረሱ፤ በሌላኛው እጃቸው እየተኮሱ አገራቸውን እየገነቡ ነው። በአንድ በኩል ከጠላት እየተከላከሉ፣ በሌላ በኩል የሰብል ምርታቸውን በብዙ እጥፍ አሳድገዋል። በዚህ ሂደትም ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ የግብርና ምርቶችን በማምረት፤ እንደ ሕዳሴ ግድብ ያሉ የተጀመሩ አገራዊ ፕሮጀክቶችን ወደላቀ ምዕራፍ በማድረስ እና ሌሎቹንም በማጠናቀቅ ሕዝባችንን ተስፋ ሊያስቆርጡ የተነሡ ጠላቶቿን ተስፋ አስቆርጣለች። በዚህም የአገር ክብርና ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ እንዲል ተደርጓል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የልማት ሥራዎችን እያጧጧፉ ጎን ለጎን የተከፈተባቸውን ጦርነት ሲመክቱ፤ ዐዋቂ እና ወጣት አትሌቶቻችን ደግሞ በዓለም አደባባይ በአገር ፍቅር ስሜት ተናበው የአገራቸውን አሸናፊነት ለወዳጅም ለጠላትም ዐውጀዋል። ሰንደቅ ዓላማችንን ከፍ አድርገው አውለብልበዋል። ከአገር አልፈው የአፍሪካ ኩራት ሆነዋል።

ኢትዮጵያችን በብዙ ፈተና በተወጠረችበት በዚህ ወቅት ጠላቶቿን እየመከተች የልማት ሥራዎችን በታላቅ ስኬት ቀጥላበታለች። የምግብ ሉዓላዊነት ሳይኖር የአገር ሉዓላዊነትን ማስከበር ከባድ ነው። በልመና ስንዴ የሰንደቅ ዓላማ ክብርን በዘላቂነት ማረጋገጥ አዳጋች ነው። ጀግኖቻችን በጦር ግንባር በደም ያስከበሯትን ሰንደቅ ዓላማ፤ በልማት ትግል በላባችን ከፍ ለማድረግ፣ ሁሉም በተሠማራበት መስክ የበኩሉን መወጣት ይኖርበታል።

**ጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

### በሰሜን ኢትዮጵያ የሚካሄደውን የመከላከል ርምጃ በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

በአሁኑ ወቅት በሰሜን ኢትዮጵያ የተፈጠረው ግጭት፤ ሕወሓት ነሐሴ 18 ቀን 2014 ዓ.ም በሙሉ ዐቅሙ የከፈተውን ጥቃት ተከትሎ የመጣ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው። ይህም የኢትዮጵያ መንግሥት በሚያዝያ ወር ያወጀውን በሰብአዊነት ላይ የተመሠረተ የተኩስ አቁም የጣሰ ነው። የመንግሥት ጥረት ምንም ዋጋ ስላልተሰጠው፣ ሕወሓት በሁለት ዓመት ውስጥ ሀገሪቱን ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ግጭት አስገብቷታል።

ሕወሓት ሦስተኛውን ግጭት የከፈተው በአፍሪካ ኅብረት በኩል በሚደረገው የሰላም ንግግር፣ ያለ ቅድመ ሁኔታ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ላይ ለመነጋገር የኢትዮጵያ መንግሥት ዝግጁነቱን ከገለጠ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለልዩ መልዕክተኞችና መቀመጫቸውን በአዲስ አበባ ላደረጉ ዲፕሎማቶች ጥቃት ለመሠንዘር ሕወሓት ያለውን ዝግጁነት አመልክቶ ነበር።

ሕወሓት ለተለያዩ ዓለም አቀፍ አካላት በበተነው ደብዳቤ ላይ ይሄንን ጥቃት የመክፈት ፍላጎቱን በግልጽ አመልክቷል። በመሆኑም አሁን ለተፈጠረው ችግር ሁሉ ብቸኛ ተጠያቂው ሕወሓት መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ጊዜና ቦታ ከተሰጠውም ሌላ ዙር ግጭት እንደሚፈጥር ከሰሞኑ መግለጫዎቹ ለመረዳት ይቻላል።

ሕወሓት በሙሉ ዐቅሙ ጥቃት ከመክፈቱ በፊት የኢትዮጵያን የአየር ክልል ደጋፊዎቹ በሆኑ የኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ሲያስደፍር ቆይቷል። በዚህም የተነሣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የመጠበቅ ግዴታውን እንዲወጣ አስገድዶታል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስዳቸው ርምጃዎች የግድ አስፈላጊ የሆኑት በሕወሓት ተደጋጋሚ ጥቃት የተነሣ ብቻ ሳይሆን ከሀገሪቱ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅቶ በሚፈጽማቸው ተግባራት ምክንያት ጭምር ነው። ስለሆነም የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር የኢትዮጵያ መንግሥት የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የፌዴራል ተቋማትንና ታላላቅ መሠረተ ልማቶችን የግድ መጠበቅ አለበት ማለት ነው።

ይህም የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በተለይም የአየር ክልልን በሚገባ ከማስከበር አንጻር መጠበቅን የግድ አድርጎታል።

እነዚህ ተግባራት መፈጸሙ መንግሥት ሰብአዊ ርዳታን ለተረጂዎች በተገቢው ሁኔታ እንዲያሣልጥ የሚረዳው ይሆናል። በአንድ በኩል እነዚህን ዓላማዎች እያስፈጸመ በሌላ በኩል ደግሞ በአፍሪካ ኅብረት አማካኝነት ለሚካሄደው የሰላም ውይይት ዝግጁ መሆኑን የኢትዮጵያ መንግሥት በድጋሚ ያረጋግጣል። ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ሁለንተናዊና በንግግር ላይ የተመሠረተ ስምምነት አስፈላጊ መሆኑን መንግሥት ያምናል።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አግባብነት ባላቸው አሠራሮችና በዓለም አቀፍ የሰብአዊ ሕጎች በጽኑ የሚገዛ መሆኑን መንግሥት ግልጽ ለማድረግ ይፈልጋል።

ንጹሐን እንዳይጎዱ ለመከላከል እንዲቻል የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ጦርነቱ በከተሞች ውስጥ እንዳይደረግ ጥንቃቄ እያደረገ ይገኛል። ይሄንን በጽኑ ለመፈጸም እንዲቻልም ለሁሉም ተዋጊ አሐዶች ጥብቅ መመሪያ ተላልፏል።

ከዚህም ባሻገር በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በሆኑ አካባቢዎች ሰብአዊ ርዳታ በተሻለ መንገድ መቅረብ እንዲችልና የርዳታ ሠራተኞች ደኅንነት የተጠበቀ እንዲሆን መንግሥት ከርዳታ ድርጅቶች ጋር አብሮ ለመሥራት ዝግጁ ነው። ሕወሓት ንጹሐንን እንደ ጦር መከላከያ የመጠቀምና ሲቪል ተቋማትን ለወታደራዊ ሠፈርነት የመጠቀም የቆየ ልማድ አለው።

ስለሆነም ሕዝቡና የርዳታ ሠራተኞች ራሳቸውን ከሕወሓት ወታደራዊ ተቋማት እንዲያርቁ የኢትዮጵያ መንግሥት ጥሪ ያደርጋል። የርዳታ ሠራተኞችን ጨምሮ በሲቪሎች ላይ ለሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት መንግሥት ኀዘኑን በዚህ አጋጣሚ ይገልጣል። እውነቱን ለማወቅና ያልተገደበ የርዳታ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል ጉዳዮች ከተከሠቱ የሚያጣራ ይሆናል።

በመጨረሻም፣ በትግራይ ክልል የሚገኙ ዜጎቹን ደኅንነት ለመጠበቅ በሕግ የተሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን ለመወጣት የኢትዮጵያ መንግሥት ያለውን ዝግጁነት በዚሁ አጋጣሚ ያረጋግጣል።

**ጥቅምት 7 ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

# ነፃ ሃሳብ

# የሚሻለን የተሻለውን መምረጥ ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የሚሻለን ምንድነው? እንደ አገር፣ እንደ ማህበረሰብ የሚጠቅመን ምንድ ነው? አሁን ላለችው አገራችን፣ አሁን ላለው ፖለቲካና ፖለቲከኛ የሚበጀን ምንድ ነው? የሚጠቅመንን እስካላወቅን ድረስ በማይጠቅሙን ነገሮች ውስጥ መኖራችን ግድ ይሆናል። አሁን ላለንበት ወቅታዊ ሁኔታ ምን ሊጠቅመን እንደሚችል ማወቅ አገራችንን ሊታደግልን የሚችል የመጀመሪያው መልካም ውሳኔ ነው። በማይጠቅሙን ብዙ ሀሳቦች ላይ ተነጋግረንና ውሳኔ አሳልፈን እናውቃለን፤ መልካም ያልናቸው እነዛ ሀሳቦች ግን ሲረዱን አልታዩም። አሁን ከአሸባሪው ትህነግ ሆነ ከውጪ ጫናዎች አገራችንን የምንጠብቅበት ጊዜ እንጂ በከሰረ ሀሳብ እርስ በርሳችን የምንናቆርበት አይደለም።

የሚሻለን የተሻለውን መምረጥ ብቻ ነው። የተሻለው ነገር ደግሞ የተሻለ አገር ሊፈጥር የሚችል ሀሳብ፣ እውቀት፣ ምክክር፣ ንግግር፣ ሰላም፣ አንድነት ነው። አገር ሊጠቅሙ የሚችሉ ቁም ነገር አዘል ሀሳቦችን ወደ ጎን ብለን በማይጠቅሙን የሰፈር ወሬዎች ላይ ተጠምደን ብዙ እድሎቻችንን ገፍተናል። አጀንዳ ሊያዝላቸው ቀርቶ ሊደመጡ እንኳን በማይገባቸው አሉባልታዎች ላይ ተጠምደን የአንድ ትውልድ ያክል እድሜ አባክነናል። አሁን በነቃና በተቆጨ ልብ የሚሻለንን የምንመርጥበት ጊዜ ላይ ነን።

ከአሸባሪው ትህነግ ውንብድና መርጦ በተወናበደ አስተሳሰብ ለሀያ ሰባት ዓመት የተወናበደች አገር ፈጥሯል። አሁንም በእውቀትና በአስተውሎት ባልጠራ አካሄድ እንደ ትላንቱ አንድ ቦታ እየረገጠ በአንድ አይነት ድርጊት ውስጥ ይገኛል። እኛስ ምን መረጥን? አገር ወዳድ ነን የምንለው እኛ የነውረኞችን ሀሳብ ተረት የሚያደርግ ሀሳብና አንድነት ያስፈልገናል። ቡድኑ ከምዕራባውያን ጋር ነው። እንደሱ ጭካኔና ውንብድናን በተላበሱ ሸኔና አልሻባብ ጋር ነው። የኢትዮጵያን መፍረስና መውደቅ ከሚመኙት ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ነው። እኛስ ከማን ጋር ነን?

እኛ ከራሳችንና ኢትዮጵያን ከሚያፈቅሩ ወንድሞቻችን ጋር ልናብር ይገባል። እውነትን ሽተው ስለኢትዮጵያ ከሚጮሁ አንደበቶች ጋር ልንቆም ይገባል። የኢትዮጵያን ሉአላዊነት አሳልፌ አልሰጥም ብሎ ብዙ ጫናና አድሎ እያስተናገደ ካለው ከመንግስት ጎን ልንቆም ይገባል። ባገኘነው አጋጣሚ ሁሉ አገራዊ ክብራችንን ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉ አጋጣሚዎች ውስጥ መሆናችንን መረዳት ይኖርብናል። ከሰሞኑ አሸባሪውን ትህነግ በመቃወም የትግራይ ተወላጆች አደባባይ ወጥተዋል። መነሻቸውን ከአራት ኪሎ በማድረግ ሸሮ ሜዳ በሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ፊት አሸባሪ ቡድኑን በመቃወም ከነመፈክራቸው ድምጻቸውን አሰምተዋል። ቡድኑ ለትግራይ ህዝብ አስቦ እንደማያውቅና ለራሱ ሲል የድሀ ልጆችን እያስጨረሰ እንደሆነ ተቃውሟቸውን ገልጸዋል። ትግራይ ጦርነት ሳይሆን ሰላም እንደሚያስፈልጋትና ቡድን ግን ደግሞ የሰላም አማራጮችን ረግጦ ንጹሀንን እያስጨረሰ እንደሆነ በመግለጽ የአሜሪካ መንግስት በቡድን ላይ ርምጃ እንዲወስድ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

የሚሻለን የሚሻለውን መምረጥ ነው። ልክ እንደ ትግራይ ተወላጆች ሁሉ ስለ አሸባሪው ትህነግ እዚም እዛም መጮህ ያስፈልጋል። ከሰላም የበለጠ የሚሻለን አልነበረም። ከውይይትና ከምክክር በላይ የሚያስፈልገን አልነበረም። መንግስት ይሄን ሲመርጥ ቡድኑ ግን ይሄን አልመረጠም። ምክንያቱም አሸባሪ ቡድን ስለሆነ በሰላምና በመመካከር ውስጥ የሚያተርፈው የለም። ብቸኛ አላማው ስልጣንና ኢትዮጵያን ለእሱ እንደምትመች አድርጎ መፍጠር ስለሆነ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን፣ ከምክክር ይልቅ ፉክክርን መርጦ የሚንቀሳቀስ ነው። እንደዛማ ባይሆን በዚህ ልክ በባልተሰቃየን ነበር። ሰሞኑን ከአንድ የፖለቲካ ምሁር ያደመጥኩት አንድ ደስ የሚል እውነት ነበር ... አሸባሪውን ትህነግ ሲገልጡን እንዲህ ነው ያሉት ‹ሕወሓት ካለጦርነት መኖር የማይችል ቡድን ነው። በጦርነት ተወልዶ በጦርነት ስላደገ የሰላምን ዋጋ አያውቀውም። ዛሬ ላይ በንጹሀን ላይ ይሄን ያክል ዘግናኝ ግፍ የሚያደርሰው፣ ለትውልድ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ባንክ ቤቶችን የሚያፈርሰው፣ ምንም የማያውቁ ህጻናትን የሚገለው፣ ሴቶችን የሚደፍረውና አረጋውያንን የሚያሰቃየው ህዝብ በመንግስት ላይ እንዲነሳ በማሰብ ነው“ ሲሉ።

የትኛውም ዜጋ ለቡድኑ እኩይ አላማ ማስፈጸሚያ እንዳንሆን ራሳችንን መጠበቅ አለበት። የአሸባሪውን ትህነግ እና የጀሌዎቹን እኩይ አላማ ተረድቶ ኢትዮጵያን ለአውሬዎች አልሰጥም ካለው መንግስት ጎን መቆም ይጠበቅብናል። የሚሻለን አንድና አንድ ኢትዮጵያን ከሚያፈቅሩ መልካም ልቦች ጎን መሰለፍ ነው። እዛም እዚም የምንሰማቸው ሞትና መፈናቀሎች ቡድኑ ሆን ብሎና አስቦበት በህዝብና በመንግስት መካከል ልዩነትን ለመፍጠር የሚያደርገው የተንኮል ርምጃ ስለሆነ ለዚህ እኩይ አላማው ማራመጃ እንዳንሆን ራሳችንን በማስተዋል መከበብ አለብን። ሙህሩ እንዳሉት..በሰላም በመነጋገር ጦርነትን ማስቀረት እየተቻለ ግን ደግሞ አሸባሪው ትህነግ ጦርነትን የመረጠበት አንዱና ዋነኛ ምክንያት በህዝብና በመንግስት መካከል አለመተማመንን ለመፍጠር ነው። ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት አጣ ማለት የቡድኑ ጊዜ ነው ማለት ነው። ቡድኑ ህዝብና መንግስትን ሆድና ጀርባ አድርጎ የስልጣን መደላድሉን አቋራጭ ማድረግ ይፈልጋል። ለዛም ነው ሸኔንና አሸባሪ ቡድኖችን አሰማርቶ ብዙ ሞትና እንግልቶችን እየፈጠረ ያለው።

አሸባሪው ትህነግ መች ጦርነት መጀመር እንዳለበት፣ መች ማቆም እንዳለበት በስሌት ውስጥ ነው። ርምጃው ሁሉ ኢትዮጵያን ወደሚጎዳ ነው። መች ገርፎ ማልቀስ እንዳለበት፣ መች ዋሽቶ ማስመሰል እንዳለበት ያውቃል። አርሶ አደሩ ምርት የሚሰበስብበትንና ምርት የሚያመርትበትን ጊዜ እየጠበቀ ነውጥ ሲፈጥር ነበር..ኢትዮጵያን ለማፍረስ፣ ኢትዮጵያን ለማስራብ ብዙ ለፍቷል.. በአንድነት ድምጾች ግን አልተሳካለትም። አሁንም እንዳይሳካለት ለማድረግ የሚሻለንን መምረጥ አለብን። ለቡድኑ የማይመች ወጣትና ህዝብ መፈጠር አለበት። አምኖ የሚጠይቅ ሳይሆን ጠይቆ የሚያምን ትውልድ አገራችን ትሻለች።

ቡድኑ ስለመረጠ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ያዋጣኛል ያለውን ሁሉንም አማራጭ እየተጠቀመ ነው። ከውጪ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ አንዳንድ አገራትንና ዓለም ዓቀፍ ተቋሚትን፤ ከአገር ውስጥ አሸባሪው ሸኔና ሌሎች አሸባሪ ቡድኖችን በመጠቀም በኢትዮጵያ ላይ ኪሳራ ለማድረስ እየለፋ ነው። የእስከዛሬ የአንድነት ጽናታችን በርትቶ አላማውን እንዳያሳካ አድርገነዋል። ባለፉት የስልጣን ዘመኑም ቢሆን ኢትዮጵያን ከመጥቀም ይልቅ ራሱን በመጥቀም ስራ ላይ ነበር ያሳለፈው። ስልጣንና ብሄርተኝነትን መሰረት ባደረገ የፖለቲካ ፍልስፍና ለሶስት አስርት ዓመታት አገራችንን ወደ መቀመቅ የከተተ ሆኖ አልፏል። ሸኔ ሕወሓት በሀያ ሰባት ዓመት የስልጣን ዘመኗ አምጣ የወለደችው የበኩር ልጇ ነው። ዛሬ ላይ ኢትዮጵያን በማፍረስ ዘመቻ ላይ ቀኝ እጇ ሆኖ እያገለገላት ያለው የዛ ዘመን ውለታውን እየከፈለ ነው።

> **ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት አጣ ማለት የቡድኑ ጊዜ ነው ማለት ነው። ቡድኑ ህዝብና መንግስትን ሆድና ጀርባ አድርጎ የስልጣን መደሳድሉን አቋራጭ ማድረግ ይፈልጋል። ለዛም ነው ሸኔንና አሸባሪ ቡድኖችን አሰማርቶ ብዙ ሞትና እንግልቶችን እየፈጠረ ያለው**

ከአሸባሪው ትህነግ ከውሸትና ከጭካኔ ወጥቶ አያውቅም። መሰረቱ በንጹሀን ደምና እንግልት የጸና ነው። ገሎና አጭበርብሮ ወደ ስልጣን መጣ። አሁንም በመግደል ወደ ስልጣን ለመምጣት እየባዘነ ነው። ሁሉን ትተን ያለፉትን ሁለት ዓመታት ብናስተውል እንኳን ለማመን የሚከብዱ ውሸቶችንና ነውሮችን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ፈጽሟል። ይሄ ቡድን በብዙ ውሸትና በብዙ ጨካኝ ወንበዴዎች የተዋቀረ ነው። አላማው ሰላም ቢሆን ብዙ የሰላም አማራጮች ነበሩት። ግን አይደለም..አላማው ኢትዮጵያን ማፍረስ ስለሆነ የሰላም አማራጮችን ሳይቀበል ቀይቷል። ይሄን ቡድን የምንነቅለው የሚሻለንን ስናውቅ ብቻ ነው። የሚሻለን ደግሞ አንድነትና ወንድማማችነት ነው። የሚሻለን ስለአገራችን አንድ አቋም ይዘን በይበቃል ስንጮህ ነው። የሚሻለን የሚሻለውን ስናውቅ ነው።

አሁንም ቢሆን ቡድኑ ወደ ሰላም ድርድር እንዲመጣ እድሎች አሉት። የእስከዛሬውን የመንግስትን ጥሪ ትተን የሰሞኑን የአፍሪካ ህብረትን የሰላም ጥሪ ብናይ እንኳን ቀድሞ የይሁንታ ምላሽ የሰጠው የኢትዮጵያ መንግስት ነው። የአፍሪካ ህብረት የሰላም ምክክሩን የሚመሩ አካላትን ጨምሮ የትና መቼ የሚለውን ገልጾ የሰላም ውይይቱ እንዲጀመር ለሁለቱም ተፋላሚ ቡድን (ለሕወሓትና ለፌደራል መንግስት) ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል። በዚህ ጥሪ ላይ ምላሽ በመስጠት ለሰላም ጥሪው ያለውን አቋም በመግለጽ መንግስት ቀዳሚው ሆኗል። መንግስት የትም መቼም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለሰላም ቅድሚያ መስጠቱን በብዙ አቅጣጫ ልናየው እንችለዋለን። የዜጎችን ሞትና እንግልት ለማስቀረት ከማሰብም በላይ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እንደሚፈቱ በማመንም ጭምር ነው። መንግስት ለአገርና ህዝብ ቅድሚያ መስጠትን ከምናይበት መንገድ አንዱ ከአሸባሪ ቡድን ጋር ለሰላም ድርድር መቀመጡ ነው።

የሚሻለን ምንድነው? ይሄ ለፖለቲከኞቻችንም ሆነ ለፖለቲካችንም ወሳኝ ጥያቄ ነው። የሚበጀን ምንድነው? ይሄ አሁን ላለነው ኢትዮጵያን እንወዳለን ለምንለው ለእኔና ለእናንተ ወሳኝ ጥያቄ ነው። ለሚመጣውም ሆነ ላለውም ትውልድ ወቅታዊ ጥያቄ ነው። የሚሻለንን ማወቅ አለብን። የሚጠቅመንን.. የሚበጀንን መለየት አለብን። በተመረጡ ሀሳቦች፣ በተመረጡ እውቀቶች የምንከባከብበት ወቅት ላይ ነን። አገራችን በሰላም ውስጥ ተጸንሳ እንድትፈጠር የሰላም ሰዎች መሆን የመጀመሪያው ውለታችን ነው። ሰላምን እንደ ትልቅ የእውቀትና የስልጣኔ በትር አድርገን ነውጥ ፈጣሪዎችን በመቃወም አደባባይ መውጣትን መለማመድ አለብን።

አገር በሰላም ውስጥና ከሰላም ውጪ ባሉ ጽንሰ ሀሳቦች ውስጥ የተለያየች ናት። በሕወሓት ውንብድና ያሳለፍናቸው አስራ ሁለት የመከራ ወራቶች አገራችንን ምን ያክል ዋጋ እንዳስከፈላት ሁላችንም የምናውቀው ሀቅ ነው። በብዙ ነገር የደከምንበት ወቅት ነው። አሁን ላይ ለተፈጠሩብን የህይወት ምስቅልቅሎች ተጠያቂው ሕወሓት ነው። ይሄን ቡድን የምናሸንፈው ደግሞ የሚሻለንን ስናውቅ ብቻ ነው..የሚሻለን ደግሞ ባለአገር መሆን ነው።

አገራችንን በተመለከተ ሁለት ምርጫዎች አሉን.. ራሳችንን በእውቀትና በምክንያታዊነት አጅበን ጠላቶቻችን የማይችሉን ማድረግ ወይም ደግሞ ሳንጠይቅና ሳንረዳ በውሸታሞች ተረትተን ለክፉ ሀሳባቸው መጠቀሚያ መሆን ነው። ወቅቱ ራሳችንን በእውቀትና በምክንያታዊ ሀሳቦች ከበን ለክፉዎች የማይመች እንድንሄድ የሚጠይቅ ነው። አሸባሪ ቡድን ተስፋ እንደሌለው ሊገባን ይገባል። ተስፋ ያለው ኢትዮጵያን ብለው በቆሙ ልቦች ውስጥ ነው። እናም ኢትዮጵያን ብለን እንቁም..። የሚሻለን ይሄ ነውና።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# የሳይበር ደህንነት፡ የሉዓላዊነት ማስከበሪያና የህልውና ማስጠበቂያ

**አንተነህ ቸሬ**

በአሁኑ ወቅት የሳይበር ደህንነት የዓለም አገራት ብሔራዊ ጥቅማቸውንና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ በሚያደርጓቸው ጥረቶች ትልቅ ትኩረት እየሰጧቸው ካሉ ጉዳዮች መካከል አንዱ ሆኗል። ከዚህ ባለፈም የሳይበር ዘርፍ አገራት የቴክኖሎጂ የበላይነታቸውን ለማሳየት ጭምር የሚጠቀሙበት መሳሪያም እየሆነ ነው። በፖለቲካና ምጣኔ ሀብት ጉዳዮች አለመግባባት ውስጥ የገቡ አገራት አንዱ የፍልሚያ ግንባራቸው የሳይበሩ ዘርፍ ሲሆን መመልከት ተለምዷል። አገራት በሳይበር ቴክኖሎጂ ዘርፍ ልቆ በመገኘት በሌሎች አገራት ላይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ስነ ልቦናዊ ጫና ለመፍጠር እልህ አስጨራሽ ፉክክር እያደረጉ ናቸው።

አብዛኞቹ ታዳጊ አገራት የሚጠቀሟቸው የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂዎች ከበለፀጉ አገራት በግዥና በድጋፍ የሚያገኟቸው በመሆናቸው፣ የቴክኖሎጂዎቹ ባለቤት ለሆኑት አገራት የእጅ አዙር ቅኝ ተገዢ እንዲሆኑ እያስገደዳቸው ነው። በአፍሪካ የተፈጠረው የሳይበር ደህንነት የአጠቃቀም ክፍተት እና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት አህጉሪቱ በየዓመቱ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ እንድታጣ እያደረጋት እንደሚገኝ መረጃዎች ያሳያሉ።

የሳይበር ምኅዳር ዓለም አቀፍ ሉላዊነት እንዲፈጠር ያደረገ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ ከሳይበር ምኅዳር ውጭ መሆን የማይታሰብ ሆኗል። ያለ ሳይበር አቅም እንደአገርም ሆነ እንደተቋም ተወዳዳሪ ሆኖ መዝለቅ ይቅርና ህልውናን ማስጠበቅ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። በአጠቃላይ ውጤታማ የሳይበር ቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ያላረጋገጠና የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት ያላስጠበቀ አገር ሉዓላዊነቱንና ብሔራዊ ጥቅሙን ማስጠበቅ የማይችልበት ወቅት ላይ ተደርሷል።

የሳይበር ምህዳር የተለያዩ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን መሰረተ-ልማቶች ማለትም ኮምፒውተሮች፣ ራውተሮች፣ የኮምፒውተር ኔትዎርኮች፣ ወ.ዘ.ተ. ተሳስረው የፈጠሩት ምናባዊ ዓለም ሲሆን በዚህ ምህዳር ውስጥ ኢንፎርሜሽን ይቀመጣል፣ ይሰራጫል፣ እንዲሁም ይተነተናል። ሳይበር በባህሪው ድንበር የማይገድበው፣ ውስብስብ እና ኢ-ተገማች በመሆኑ በአሁኑ ወቅት የአንድን አገር ሉዓላዊነት ከሚፈታተኑት አበይት ጉዳዮች መካከል አንዱ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ሆኗል።

የሳይበር ጥቃት በኮምፒውተር ስርዓቶች፣ መሰረተ-ልማቶች እና ኔትዎርኮች ላይ ሆን ተብሎ ያልተፈቀዱ አጥፊ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም በህገ ወጥ መንገድ መረጃዎችን የመበዝበዝ እና አገልግሎት የማስተጓጎል ተግባር ነው። የሳይበር ጥቃቶች በአብዛኛው የኮምፒውተር ስርዓቶችንና እና የመጠቀሚያ መሳሪያዎችን ክፍተት በመጠቀም የሚሰነዘሩ ናቸው። በማህበራዊ የትስስር-ገፆች ላይ ደግሞ ከባህልና ከስነ-ምግባር ውጪ ባፈነገጠ መንገድ ከሚለጠፉ ምስሎች እና መልዕክቶች ጀምሮ የመረጃ መረብን ተገን በማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈፀሙ የመረጃ ስርቆቶች የሳይበር ጥቃት ማሳያዎች ናቸው።

የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን ለመከላከል ሊወሰዱ ከሚገቡ የጥንቃቄ እርምጃዎች መካከል ከማይታወቁ አካላት ለሚላኩ የኢ-ሜይል መልእክቶች ምላሽ አለመስጠት፤ በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ዝርዝር ግላዊ መረጃዎችን አለማጋራት፤ ህጋዊ ያልሆኑ ሶፍትዌሮችን አለመጠቀም፤ የመረጃ ማከማቻ ቁሶችን (እንደ ፍላሽ፣ ሀርድዲስክ...) አካላዊ ደህንነት መጠበቅ እንዲሁም የህዝብ ዋይፋዮችን አለመጠቀም ይጠቀሳሉ።

የኢትዮጵያ የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትም በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያሳያሉ። በ2012 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ የተሞከረው የሳይበር ጥቃት አንድ ሺህ 80 ነበር። ጥቃቱ በ2013 ዓ.ም ወደ ሁለት ሺ 800 ከፍ ብሏል። በ2014 ዓ.ም ደግሞ ስምንት ሺ 900 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን፣ ይህ አሀዝ ከቀደሙት ዓመታት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ጭማሪ አሳይቷል። በ2015 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመትም አንድ ሺ 613 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ተመዝግበዋል።

በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ ከስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ እና አሸባሪው ሕወሓት ከከፈተው ጦርነት ጋር ግንኙነት ያላቸው ሲሆን፤ የመገናኛ ብዙኃን እና የፋይናንስ ተቋማት እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የጥቃት ሙከራዎቹ ኢላማዎች ናቸው።

ከእነዚህ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች አሃዝ መረዳት የሚቻለው በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘሩ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች በየዓመቱ እየጨመሩ መምጣታቸውንና ይህን ታሳቢ ያደረገ የሳይበር ደህንነት ጥበቃ ተግባር እንደሚያስፈልግ ነው። የ2014 ዓ.ም አገራዊ የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖርትም የአገሪቱ ተቋማት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ለወቅቱ የሚመጥን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በመተግበር ለሳይበር ደህንነት ትኩረት መስጠት እንደሚገባቸው ምክረ ሃሳቦችን አቅርቧል። በዚህ ረገድ የደህንነት ስትራቴጂዎችን አስቀድሞ ማዘጋጀት የሳይበር ጥቃቶች የሚያደርሱትን ኪሳራ መከላከል እንደሚያስፈልግ አቅጣጫዎችን ጠቁሟል።

የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ማሳደግ አገራዊ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። በዚሁ መሰረት የተቋማትን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ንቅናቄዎችን ለማከናወን፤ በአገራዊ የሳይበር ደህንነት ዘርፍ ላይ የግሉን ዘርፍ ሚና ለማሳደግና ለማበረታታት፤ በቂ እና ጥራት ያለው የሳይበር ደህንነት የሰው ኃይል ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር፤ እና የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን ለመተግበር ያለመው ሦስተኛው ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ወር ጥቅምት አንድ ቀን 2015 ዓ.ም መከበር ጀምሯል። ‹‹የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለአገር ሉዓላዊነት›› በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ያለው ሦስተኛው ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ወር፤ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ የሚዘልቅ ሲሆን፤ የተቋማትን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነት የመቀነስና የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ የማሳደግ ዓላማ እንዳለው ተገልጿል። ይህ የሳይበር ደህንነት ወር በተለያዩ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮች ይከበራል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በሦስተኛው አገራዊ የሳይበር ደህንነት ወር ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ላይ እንደተናገሩት፣ የሳይበር ደህንነት የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ በመሆኑ ከቴክኖሎጂ ልማቱ እኩል ለደህንነቱም ትኩረት ተሰጥቶታል።

‹‹የሳይበር ጥቃት የዓለማችን የወቅቱ የሥጋት ምንጮች ከሚባሉት አንገብጋቢ ጉዳዮች መካከል አንዱ በመሆኑ መንግሥት የሳይበር ደህንነትን ማስጠበቅ ቁልፍ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ አድርጎ እየሠራበት ይገኛል›› ያሉት ምክትልና ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፤ የሳይበር ቴክኖሎጂ ደህንነት ለኢትዮጵያ ዕድገት ስኬት ዋነኛ አውታር መሆኑን በመረዳት ከ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድ ዋና ዋና ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች መካከል አንዱ ተደርጎ በመሠራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል።

በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና መሰል ተቋማት ውስጥ በሳይበሩ ዘርፍ የአገሪቱ የመወዳደር አቅምና ተስፋ የሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን ኮትኩቶ ለማሳደግ የሚያስችሉ ማዕከላት ተቋቁመው አመርቂ ውጤት ማሳየት መጀመራቸው ተስፋ ሰጪ ጥረት መሆኑንም ጠቁመዋል። የኢትዮጵያን የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ በዋነኝነት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተሰጠ ቢሆንም የሳይበር ደህንነት ውጤታማ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑንም ነው ያስታወቁት። አገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ብሎም የሳይበር ደህንነትን እውን ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ሚና ወሳኝ እንደሆነ ገልፀዋል። ‹‹የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት አንዱ መገለጫ የሳይበር ምህዳሩ በመሆኑ በትብብርና በቅንጅት መሥራት ይገባል። ከዚህ አኳያ የሳይበር ዲፕሎማሲ ሥራችን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተን የምንሰራበት መስክ ነው። የሳይበር ደህንነት ወር የባለድርሻ አካላት ቅንጅትን ለማጠናከር እና በጋራ አላማ ላይ ተመስርቶ ለመተባበር የሚያስችል ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር መድረክ በመሆኑ በውጤታማነት ልንጠቀምበት ይገባል›› ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ በበኩላቸው የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ካስቀመጣቸው አስቻይ ሁኔታዎች ውስጥ የመረጃ መረብ ደህንነት አንዱ መሆኑን ተናግረው፤ የዲጂታል መሰረተ ልማቶችን ከጥቃት መከላከል ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና በዲጂታል ክህሎት እና በመረጃ መረብ ደህንነት ላይ የመንግስት እና የግሉ ዘርፍ ተቋማት በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የኢትዮጵያን የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ በዋነኝነት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (Information Network Security Administration - INSA) የተሰጠ ኃላፊነት ነው። ተቋሙ በአገር ደረጃ የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ጥረቶችን ከማቀናጀት እና ከመምራት በላይ በየተቋማቱ የኢንፎርሜሽን ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚረዳ ባህል እንዲዳብር፣ መሰረተ ልማቶች እንዲገነቡ እና አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ የሚያግዙ ስራዎችን ያከናውናል። ኤጀንሲው ጥቃቶች ከመታሰባቸው ጀምሮ ክትትል በማድረግና ለይቶም በመተንተን ምላሽ ይሰጣል።

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢትዮጵያን የሳይበር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ባከናወናቸው ተግባራት አገርን ከከፍተኛ ኪሳራ መታደግ እንደተቻለ የአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ ይናገራሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና በዘላቂነት በማሳደግ የአገርን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅና የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። ለአብነት ያህል በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ የተሞከሩ የሳይበር ጥቃቶችን በማክሸፍ በቢሊዮን ብር የሚገመት ኪሳራን መከላከል እንደተቻለ ጠቁመዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የዜጎች የግንዛቤ ማነስና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ለሳይበር ጥቃቶች መበራከት ጉልህ አስተዋፅኦ አላቸው። በመከበር ላይ ያለው አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት ወር የተቋማትን የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን የመቀነስ፣ በሳይበር ደህነንት ዘርፍ የግሉን ዘርፍ ሚና የማሳደግና የማበረታታት፣ በቂ እና ጥራት ያለው የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ለማፍራት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን የመፍጠር እንዲሁም የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤን የማሳደግ ዓላማዎች አሉት። በዚህ የሳይበር ደህንነት ወር ላይ የሚከናወኑ ልዩ ልዩ መርሃ ግብሮች በአጠቃላይ ከ10 ሚሊየን በላይ ዜጎችን ተደራሽ ያደርጋሉ።

አገራት የዜጎቻቸውን ብሎም የተቋሞቻቸውን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ሕሊና ለማሳደግ የሚያስችሉ የሳይበር ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብሮችን እንደሚያዘጋጁ የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ንቃተ ህሊና ዘላቂ በሆነ መልኩ ማሳደግና የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ማረጋገጥ ለሳይበር ደህንነት አስተማማኝ ዋስትናዎች እንደሆኑ ተናግረዋል።

ያለንበት ዘመን ከሳይበር ምህዳር ውጭ መሆን የማይቻልበት ሆኗል። ታዲያ በዚህ ዘመን በተቋምም ሆነ በአገር ደረጃ በሳይበር ደህንነት ዘርፍ ተወዳዳሪ መሆን ካልተቻለ አገራዊ ሉዓላዊነትም ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናም ከባድ አደጋ ውስጥ እንደሚገባ አያጠራጥርም። ስለሆነም የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ግንዛቤ በማሳደግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ባለቤትነት አቅምን በማጎልበት የሳይበር ደህንነትን ማረጋገጥ፣ ሉዓላዊነትና ማስከበርና ህልውናን ማስጠበቅ ያስፈልጋል!

> **የኢትዮጵያን የሳይበር ደህንነትን የማረጋገጥ ሥራ በዋነኝነት ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተሰጠ ቢሆንም የሳይበር ደህንነት ውጤታማ እንዲሆን የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑንም ነው ያስታወቁት፡፡ አገራዊ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ለማረጋገጥ ብሎም የሳይበር ደህንነትን እውን ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ሚና ወሳኝ እንደሆነ ገልፀዋል**

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ምን ይደረግ?


አቶ ክቡር ገና


ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ

**አስመረት ብስራት**

የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በ2015 በሁለቱ ምክር ቤቶች የመክፈቻ መርሀ ግብር ላይ ባደረጉት ንግግር እንዳሉት፤ መንግስት በ2015 በጀት አመት የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋትና ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል። የምግብ ምርትን በማሳደግና አቅርቦትን በመጨመር ውጤታማ የሆነ የፊሲካልና የገንዘብ ፖሊሲን መተግበር፣ የንግድ ሰንሰለትን በማዘመን ምርት ወደ ገበያ የሚመጣበትን መንገድ ማሳለጥ፣ የገቢ አቅማቸው አነስተኛ ለሆኑና አቅመ ደካሞች ድጎማ በማድረግ የዋጋ ንረትን አሉታዊ ተጽዕኖ መቀነስ ሌላው በበጀት አመቱ በመንግስት በትኩረት ከሚሰሩ ስራዎች ውስጥ መሆኑን አንስተዋል።

በአገራችን ባለፉት አመታት የዋጋ ንረት እየጨመረ የመጣ ክስተት ሆኗል። በ2014 ዓ.ም በርካታ ጫናዎች ቢከሰቱም በኢኮኖሚ ላይ ስኬት ተመዝግቧል። ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የውጭ ምንዛሬ እድገት አሳይቷል። በአገሪቱ የተከሰተው የዋጋ ንረት በአብዛኛው ምግብ ነክ ምርቶች ላይ መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ። ጫናው እንዲበረታ የሚያደርገውም በኢትዮጵያ አንድ ሰው ከወር ከሚያገኘው ከገቢው ወደ 54 በመቶ የሚሆነውን ለምግብ የሚያወጣ በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ የምግቡ ዋጋ በተወደደ ቁጥር ለምግብ የሚያወጣው ወጪ ከ54 በመቶ በላይ እየሆነበት ሲሄድ የዋጋ ንረቱ እየከበደው እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ በምግብ የዋጋ ንረት ሳቢያ እየታየ ያለው የኑሮ ውድነትን ቢያንስ በተወሰነ ደረጃ ለመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ነው፡፡ በተለይ የምግብ ምርቶችን መጨመር ወሳኝ ነገር ስለመሆኑም የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ ከምትፈልገው የምግብ ፍላጎት 75 በመቶውን ብቻ በአገር ውስጥ ምርት የሚሸፍን ሲሆን ቀሪው 25 በመቶ ከውጭ የሚገባ ምርት ነው፡፡ ይህን ለማስገባት ደግሞ የውጭ ምንዛሪ ያስፈልጋል፡፡ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ማስገባት ቢቻል የዋጋ ንረቱ ላይኖር ይችል ነበር። ይህም ቢሆን ዘንድሮ ለምግብ ነክ ምርቶች ብቻ 3 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር ወጪ መደረጉንም መረጃው ያመለክተዋል፡፡

በያዝነው 2014 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ለ2014 ዓ.ም. የተጨማሪ በጀትን ሳይጨምር 542 ቢሊዮን ብር የወጪ በጀት በማጽደቅ ከሐምሌ 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ ሲሆን፣ ከዚህ የወጪ በጀት ውስጥ 436 ቢሊዮን ብሩ ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች እንዲሁም ከውጭ ዕርዳታ ለመሰብሰብ ታሳቢ ተደርጎ ነበር። የተቀረው ብር 106 ቢሊዮን ደግሞ በበጀት ጉድለትነት ተይዞ፣ ጉድለቱንም ከአገር ውስጥና ከውጭ ብድር ለመሸፈን ታቅዶ ነበር። በዚሁ መሠረት ከውጭ ብድር 38 ቢሊዮን ብርና 68 ቢሊዮን ብር ከአገር ውስጥ የተጣራ ብድር በመውሰድ የበጀት ጉድለቱ እንደሚሸፈን መታቀዱን ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

የአገሪቱን ማክሮ ኢኮኖሚ ጤናማ ሆኖ እንዲቀጥል ምን መሰራት አለበት? ለኑሮ ውድነቱ፣ ከጥቁር ገበያው ችግር መፍትሄው ምንድነው? ስንል የኢኮኖሚ ባለሙያዎችን አነጋግረናል።

የኢኮኖሚ ባለሙያው የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ዋና ጸሃፊ አቶ ክቡር ገና እንደሚሉት፤ የኑሮ ውድነትን ከዋጋ ንረት ጋር ስናያይዘው የቀን ከቀን የኑሮ ሂደት ጋር የሚነሳ ጉዳይ ሆኖ ነው የምናገኘው። ይህ ማለት የአንድ ዜጋ የትራንስፖርት፤ የምግብና የቤት ኪራይ ወጪን ያጠቃልላል። አንድ ሰው በአንድ ደመወዝ ብቻ ኑሮን መሸከም ሲከብደው የኑሮ ውድነት ተፈጠረ ማለት ነው።

ይህንን ችግር ለመቅረፍም በረጅም ጊዜ እቅድ ምርትን እንዴት መጨመር እንደሚቻል ማቀድ ነው። ይህም ሲባል የገኘውን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ምርት እየጨመረ ዋጋ እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን ለመፍጠር አሁን የተጀማመሩ የኩታ ገጠም የስንዴ ልማት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በዚህ ወቅት መፍትሄ ለሚሆኑ ስራዎች ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ መሆናችንን የሚናገሩት አቶ ክቡር ገና እኛ ባለንበት ሁኔታ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ሰፋፊ ኢንቨስትመንቶችን ማምጣት አልተቻለም ይላሉ። በዚህም አዳዲስ የስራ እድሎችን የመክፈት ሁኔታ ተቀዛቅዟል። ሸማቹ ማህበረሰብ መግዣ ገንዘብ በማጣት የኑሮ ሁኔታው ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሆን ያደርገዋል ማለት መሆኑን ይናገራሉ።

ገበሬውንም በትልቅ ደረጃ እንዳያመረት ከማድረጉም በላይ፤ ወደ ኢንዱስትሪ ሊያድጉ የሚችሉ ምርቶችን የሚደግፉ እንደ ማዳበሪያ ያሉ ግብአቶችን ማምጣትም ምርታማነቱን አዳጋች ሊያደርገው የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ችግሩን አሳሳቢ ያደርገዋል ይላሉ።

ይህን ችግር ለመቅረፍ የአጭር ጊዜ እቅድ መሆን ያለበት ከቁጥጥር ጋር በተያያዘ መስራትና መንግስት ደግሞ መሰረታዊ ቁሳቁሶች ላይ ድጎማ ማድረግ፤ ይህም ነገሮች እስኪረጋጉ ድረስ ማስቀጠል የሚገባው መሆኑንም ጠቁመዋል። መንግስት ይህንን ለማድረግ አቅም እንዲኖረው ድሃ ህብረተሰብ ላይ ሳይሆን አቅም አለው የሚባለው የማህበረሰብ አካባቢ የታክስ ጭማሪ በማድረግ ገንዘብ መስብሰብ አንድ አማራጭ ነው ብለዋል።

ጤናማ ማይክሮ ኢኮኖሚ የመፍጠር ስራ ይሰራል ተብሎ የተጠቀሰው ጉዳይ አንደኛው የዋጋ ግሽበቱን ወደነበረበት መመልስ ወይም ካለበት በታች መቀነስ ሲቻል ነው። አሁን ያለው የዋጋ ግሽበት ምጣኔ ባለ ሁለት አሃዝ የሆነውን ከአምስት ከፍ ብሎ ከሰባት ባይበልጥ የማይክሮ አኮኖሚው የሚሻሻልበት ሁኔታ ሊፈጥር የሚችል መሆኑን ነው ያስረዱት።

ሁለተኛው የውጭ ምንዛሪውን በማስተካከል ምርትን ለማሳደግ የሚረዱ የውጭ ግብአቶችን ማምጣት፤ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉትን ለማምጣት መጣር ነው። የዶላር ፍላጎትን እና አቅርቦትን ማጣጣም የሚቻለው ለኤክስፖርት የሚሆን ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በረጅም ጊዜ ማይክሮ ኢኮኖሚውን የሚያሻሽልበት ሁኔታ ይፈጥራል።

ሌላው ባንኮች የሚሰጡትን ወለድ ከኢንፍሌሽኑ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል። አንፍሌሽን ሰለሳ በመቶ ሆኖ የባንክ ወለድ አስር በመቶ ከሆነ ይሄ የሚስተካከልበት መንገድ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። መንግስት ከታክስም ሆነ ከተለያዩ ገቢዎች የሚያገኘው ገንዘብ ሲያጥር ከምንም ተነስቶ ገንዘብ ይፈጥራል፤ ይህም ግሽበቱን ለመቀነስ ስለሚያስችል ኑሮን ለማረጋጋት አንድ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰዋል።

የኢኮኖሚ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ በበኩላቸው፤ የኑሮ ውድነቱን ለመሻሻል መጀመሪያ ምክንያቶችን ማወቅ ያስፈልጋል ይላሉ። የኑሮ ውድነቱን ከፍ ያደረገው የብር ዋጋ ማሽቆልቆል ነው። ማህበረሰቡ የሚፈልጋቸው የምግብ አይነቶች በሚፈልጋቸው አልበሳት ከውጭ ስለሚመጡና ነጋዴው ከጥቁር ገበያ በሚያመጣው ዶላር ያስገባውን ልብስ በውድ ዋጋ ስለሚሸጥ የአገራችን ሁኔታ ልዩ እንዲሆን አድርጎታል ብለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ የእኛን አገርም አጥቀቶታል። ከኮቪድ ወቅት ጀምሮ የትራንስፖርት ሰንሰለቱ ላይ ክፍተት መፈጠሩ በገቢ እቃዎች ላይ ጫናን ፈጥሯል። አገሪቱ የምታርሰው መሬት በቅርብ ጊዜ እየተሻሻለ ከመሆኑ በስተቀር 26 ሚሊየን ህዝብ በነበረበት ጊዜ የሚታረሰው እርሻና በ4 እጥፍ በጨመረበት ጊዜ ላይ ለውጥ አለመኖሩ በአገሪቱ ምርት ላይ ጫና እንዲፈጠር አድርጎታል።

ሌላው አገሪቱ የምታካሄደው ትላልቅ ፕሮጀክቶች መኖራቸው በርካታ ኢኮኖሚውን የሚደግፈው ገንዘብ ወደ ስራው መሄዱ አሳሳቢ ነው። ከላይ የጠቀስናቸው በሙሉ የኢኮኖሚ እድገት ቁስሎች በመሆናቸው የተነሳ እነሱን ከላከምን በስተቀር ችግሩ ስር መስደዱ የማይቀር ነው።

በአገሪቱ ውስጥ ያለው ከፍተኛ የሙስና ችግር በኢኮኖሚው ላይ ጫና ፈጥሯል። በተወካዮች ምክር ቤት ዋና ኦዲተሯ ሪፖርት በሚያቀረቡበት ጊዜ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ እንደባከነ ስለመሆኑ ነው የገለፁት። ይሄን ያህል ገንዘብ ሲባክንስ መንግስት ምን እያደረገ ነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ይሄ የበጀት ገንዘብ ከግብር ከህዝቡ ተሰብስቦ በድጎማ ለስራ የቀረበ ገንዘብ በመሆኑ ይሄንን መቆጣጠርም የኢኮኖሚ ጫናውን ለመቀነስ ያግዛል።

ከመልካም አስተዳደር ችግሮች የሚመጡም ሁኔታዎች መኖራቸው ይታያል። ይህም ጥቂት ነጋዴዎች ህዝቡን እንዲበዘብዙ የሚፈቀድ ከሆነ፤ መንግስት ያንን መቆጣጠር ካልቻለ ህብረተሰቡ ችግር ውስጥ ይገባል። መንግስት ግን ይሄንን ለማስተካከል እሰራለሁ ማለቱ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

መንግስት ሁኔታዎችን ለማረጋጋት ከሌሎች አገራት የቀደመ ተሞክሮ መማር ይኖርበታል የሚሉት የኢኮኖሚ ባለሙያው በኮቪድ ወቅት ትላልቅ አገራት ለዜጎቻቸው እርዳታ ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን አስታውሰዋል። መንግስትም ይሄንን ተሞክሮ በመውሰድ ማህበረሰቡ ከድህነት መረብ በታች እንዳይወርድ መስራት ይገባል።

በዋናነት አገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ ማረጋጋት፣ በሙሉ አቅም ወደ ልማት የሚገባበትን አማራጭ መፍጠር ለኢኮኖሚው መረጋጋት ቁልፍ መፍትሄ ነው። አገሪቱ አይ ኤም አፍ እንደሚለው በ5 ነጥብ 3 የኢኮኖሚው ሁኔታ ያድጋል የሚል ትንበያ መኖሩን ተከትሎ ይህ እድል የማህበረሰቡን ሕይወት ያሻሽላል ብለው እንደሚጠብቁ ይናገራሉ። ህዝቡ እንዳይጎዳ፤ ህፃናት እንዳይራቡ፣ መድሃኒት እንዳይጠፋ የአጭር ጊዜን እቅድ በማቀድ ህዝቡን መታደግ ያስፈልጋል ብለዋል።

መንግስት በአገሪቱ ያለውን ከፍተኛ የመሬትና የውሃ ሀብት በመጠቀም ምርት መጀመሩ ተስፋ ሰጪ መሆኑን

**በዋናነት አገሪቱ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ ማረጋጋት፣ ጦርነቱን አቁሞ በሙሉ አቅም ወደ ልማት የሚገባበትን አማራጭ መፍጠር ለኢኮኖሚው መረጋጋት ቁልፍ መፍትሄ ነው**

የተናገሩት የኢኮኖሚ ባለሙያው አሁን የተጀመረው ልማት ተጠናክሮ ከቀጠለ በቂ የምግብ አቅርቦት ይኖራል፤ ይሄ ደግሞ ህዝቡን ለማቆየት ያለው አስተዋፅኦ የማይናቅ መሆኑን ያብራራሉ።

ኢንዱስትሪ ፓርኮች ስራ እንዲጀምር በርካታ ኢንቨስተሮች እንዲመጡ የፋይናንስ ስርአቱን መቀየርና የውጭ ባለሃብቶችን እንዲጋብዝ ማድረግ የግድ ነው። ሌላው ችግር በአገሪቱ የካፒታል ገበያ አለመኖር ነው። ካፒታል ገበያ እንዲቋቋም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ሰጥቷል። የውጭ ባንኮችም እንዲገቡ ውሳኔ ተላልፏል። የውጭ ባንኮች ሲመጡ በአገር ውስጥ ያሉ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ይቀርፋል ብለዋል።

ከፍተኛ የመንግስት ወጪዎችን መቀነስ፣ ከብክነት የፀዳ አሰራር መስራት፤ በጠረጴዛ ስር የሚሄደውን ከፍተኛ የሙስና ሰንሰለት መበጥስ አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ። ይህንን ለማፅዳትም የምርመራ ጋዜጠኝነትን አሳድጎ ችግሮችን ለመፍታት መነሳት ለቀጣይ አገሪቱ የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖራት ለማድረግ ያስችላል።

የአፍሪካ ንግድ ምክር ቤቶች ዋና ጸሃፊ አቶ ክቡር ገና መፍትሄ ያሏቸውን ሀሳቦችን አስቀምጠዋል። ኢኮኖሚው ወደ ቦታው ተመልሶ ለኑሮ ውድነቱ መድሃኒት የሚሆነው ጦርነቱ የሚቆምበትን አማራጭ በመፍጠር ነው። አሁን ባለው ሁኔታ አገራችን ብቻ ሳትሆን በመላው ዓለም የተለያዩ ቦታዎች ጦርነቶች መኖራቸው የዓለም ኢኮኖሚ እንዲቀዛቀዝ ሆነዋል። የኛ አገርን ችግር ለመፍታት ለመነጋገር በጣም ተቸግረናል ግን ለህዝቡ ከታሰበ ጦርነቱን መቆም ነው ዋነኛው መፍትሄ። ለጦርነት የሚወጣ ገንዘብ፤ ወጣት፤ ሀሳብና ትጋት በሙሉ ለሰላም ቢሆን የተሻለ አማራጭ ነው።

ሁለተኛው ዋጋው እየናረ የሄደው የነዳጅ ዋጋ ነው። ይህ ከአገሪቱ ቁጥጥር ውጭ ነው። ምክንያቱም የነዳጅ ዋጋ በነዳጅ አቅራቢዎቹ አገራት ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው። ነገር ግን የተወሰነ ነገር በመደጎም ገበያውን ማረጋጋት ከአገሪቱ መንግስት የሚጠበቅ ነው። ለምሳሌ አቅም ያለው የሚጠቀመው ነዳጅና አቅም የሌለው በእግሩ የሚሄደው ግለሰብ በነዳጅ ምክንያት ሕይወቱ ላይ የሚመጣ ጫና አስቸጋሪ ስለሆነ ለእንደዚህ አይነት ሰዎች ድጎማ ያስፈልጋል።

ሌላው ሰው ወደ ስራ ዓለም የሚገባበትና የውጭ ኢንቨስትመንቶች ወደ አገር የሚሳቡበት ሁኔታ ማመቻቸት የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ያግዛል። ይህም ከመሬት ጋር የተገናኙ፤ ከባንክ ጋር የተያያዘና የመንግስት ህግና መመሪያን በማስተካከል የውጭ ኢንቨስትመንት መሳብ የግድ ይላል ብለዋል።

በአጠቃላይ የሲቪል ማህበራትን ማጠናከር፤ ሙስናን መከላከል፤ ማህበረሰቡን ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴ ማድረግና ለአገር እድገት በጋራ መረባረብ ለውጥ እንደሚያመጣ የዘረፉ ሙያተኞች አስረድተዋል። ካልሆነ ግን ውጭ ውጥተን ለልመና እጃችንን መዘርጋት የግድ ሊሆን እንደሚችል አሳስበዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ‹‹ማስተማር ሱሴ ነው››

- መምህርትና ደራሲ እፀገነት ከበደ

**ሰላማዊት ውቤ**

መምህርት እፀገነት ከበደ ትባላለች። መምህርት፤ ደራሲና የሚዲያ ባለሙያም ነች። በግጥም ምሽቶች መድረኮች ላይ ትታወቃለች። ሳታየር ተረቶችን በዚህ መድረክ ታቀርባለች።

‹‹ ፈጣሪ ወደዚህ ዓለም የመጡ ፍጡሮቹን እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንዳስተምራቸው የመረጠኝ በመሆኔ በስነጽሑፉ ዓለምም ሆነ በመገናኛ ብዙሃኑ ሙያ ዘርፍ መሰማራት የሚያስችል አማራጭ ቢኖረኝም ከማስተማር መነጠል አልችልም›› የሚል ዕምነት አላት። ራሴን ፈትኜ አውቃለሁ። ግን ማስተማር ሱስ የሆነበት ሰው ዓይነት ነኝ። ልጆች ላይ መሥራትና ማስተማር ሕልሜም ፍላጎቴም ነው ስትል ስለ ራሷ ትገልፃለች። ቀድሞ በነበራት ልምድ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንም ታስተምር የነበረች ቢሆንም አሁን እያስተማረችበት ያለችበት ‹ላይነርስ› አካዳሚ የውጭ ዜጎች ትምህርት ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ብቻ ስለሚያስተናግድ አሁን ላይ የምታስተምረው እስከ ስምንተኛ ክፍል ያሉ ልጆችን ነው። በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህርትና የአማርኛ ትምህርት ክፍል ኃላፊም ናት። ልጆች ላይ መሥራትና ማስተማር ስጦታዬ ነው ትላለች።

በመምህርነት ሙያ መሥራት ከጀመረች 13ኛ ዓመቷን ጨርሳ 14ኛውን የያዘችው መምህርት እፀገነት ባለቤቷም እንደ እሷ በመምህርነት ሙያ የተሰማራ ነው። ወላጆቻቸው የተለያዩባቸውንና በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የሚገኙ የአካባቢያቸው ልጆችን ትምህርትን ተቀብለው በወደፊት ሕይወታቸው ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጡ በማድረጉ ረገድ መኖሪያ ቤታቸውን ሳይቀር መስዕዋት አድርገው በጋራ በነፃ እያስተማሩ ነው። እሷ ትምህርት ቤት ስታስተምር ውላ ስትመጣ ባለቤቷ በቤታቸው ውስጥ የአካባቢውን ልጆች ከትምህርት ቤት መልስ በተለይም ትምህርት ቤት ዝግ በሚሆንበት ጊዜ በነፃ ሲያስተምር ይቆያታል። የልጆቹን የትምህርት አቀባበል ሁኔታም ሪፖርት ያደርግላታል።

መምህርቷ ልጆች በትምህርት ውጤታማ የሚሆኑበት በርካታ መጽሐፍቶች እያዘጋጀች ስትገኝ አንድ የልጆች መጽሐፍና አንድ የአዋቂዎች መጽሐፍትም አሳትማለች። አንደኛውና የ‹‹እንጎቻ ታሪኮች›› የሚለው የተረቶች ስብስብ ነው። ተረቶች ለሁለት ጉዳይ ይዘጋጃሉ። አንደኛው የንባብ ክሎታቸውን ለማዳበር ሲሆን ሁለተኛው ሞራላቸው ስነ ልቦናቸው እንዲገነባ የሚሰሩ ናቸው። ሞራላቸውን ከፍ ከማድረግ በተጨማሪ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲኖሩ የሚፈለጉና የማይፈለጉ ነገሮችን ወደ ልጆች በማስተላለፍ እንዲቀረፁ የሚደረገው በተረቶች አማካኝነት ነው። አባቶቻችንም ሲያደርጉ የነበረው ይሄንኑ ነው።

ማህበረሰቡን ቅርጽ እያስያዙ አሁን ድረስ ያመጡት በተረቶች፤ በተረትና ምሳሌዎች፤ በእንቆቅልሾች እና በስነ ቃሎች ነው። እስከ አሁን የመጣነው በዚህ መንገድ ነው። የእኛ ማህበረሰብ ዝም ብሎ ዱብ ብሎ የተገኘ ሳይሆን ብዙ የተለፋበት ነው። ‹‹የኔ ተረት ትንሽ የሚለየው ሲዲም ጭምር አለው›› የምትለው መምህርት እፀገነት የሚነበቡ ብቻ ሳይሆኑ የሚደመጡም እንደሆኑ ታብራራለች። ይሄን ያዘጋጀችው ፈረንጆች ከመተኛታቸው በፊት ወላጆቻቸው ተረቶች ታሪኮች ያነቡላቸዋል። ይሄ አንድም ልጆቹ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ቅርበት ይጨምረዋል። በተጨማሪም ምናባቸው ከፍ እንዲል አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይሄን ነገር እኛ ባህል አላደረግነውም። ወይም ከአያቶቻችን ብንወርሰውም ዘንግተንና ትተነዋል። ምንድነው ምክንያቱ ብላ የተወሰኑ ወላጆችን እንዳስተማሪ ጠይቃ ያገኘችው መልስ ቀን በሥራ እናሳልፋለን ደክሞን ነው የምንገባው የሚል ነው። ይሄ ልጆች ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ በዚህ መተካት ይቻላል ብላ ነው ሲዲውን ያዘጋጀችው። ሲዲ በዚህ ዓይነት መንገድ መጽሐፉ ከሲዲ ጋር ተጋግዞ እንዲሰራ አድርገው ነው ያወጡት። ባለቤቷም በሲዲ ዝግጅቱ የተሳተፈ ሲሆን 10 የሚሆኑ ተረቶች ይዟል። ሁሉም መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ልጆች እንዲለዩ የሚያደርጉ ናቸው።

ለምሳሌ አንዱ ሁለቱ እህትማማች ዳክየዎች የሚል ተረት ሲሆን ውሃ ለመጠጣት የሚሄዱበት መንገድ ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን አንደኛዋ ዳክየ ለሌለኛዋ ቀበሮ እንዳየችና በዛ መንገድ መሄድ እንደሌለባቸው ትነግራታለች። ሌላዋ ዳክየም ከለመድኩት ውጭ በሌላ መንገድ መሄድ አልፈልግም ትላለች። ብትለምናትም አልሰማቻትም። በመጨረሻ አብረው ይሄዳሉ። በዚህ መካከል ያለችው ተኩላ አጋጠማቸውና ከመበላት ለጥቂት ተረፉ። ይሄን ተረት ያመጣችው ሕይወት ውስጥ ብዙ አማራጮች መኖራቸውንና ይሄን ባለመጠቀማችን ችግር ውስጥ እንደምንገባ ለማሳየት ነው። አንዱ ሳይሆን ሲቀር ሌላውን መሞከር ተገቢ መሆኑን ለመጠቆምም ነው። ሌላውን መሞከር እንጂ ተስፋ መቁረጥ ለሕይወታቸው እንደማይበጅ ለማሳየት ነው።

ሌላኛው መጽሐፏ ‹‹ማለዳን መናፈቅ›› የሚልና ለአዋቂዎች የተጻፈ ሲሆን ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች አሉብን። ችግሮቻችንንና ራሳችንን የምናይበት የተለያየ መንገድ እንደሚያስፈልገን ያስተምራል በማለት በውስጡ 20 የሚደርሱ ታሪኮች ስላሉት መጽሀፏ ትናገራለች።

‹‹ልጆች በትምህርትም ሆነ በየትኛውም መንገድ ግንዛቤ መጨበጥ ያለባቸው በዕድሜያቸው መጠን ነው›› በዕድሜያቸው መጠን ቃላትን አውቀው ችግር ሲገጥማቸው ችግሮችን መፍታት ይችላሉ ባይ ናት፤ ለምሳሌ ኳስ ሲጫወቱ የሚያጋጥሙ ግጭቶችንና ኢፍትሃዊ የሆነ አካሄድ የሚፈቱበትን መንገድ ማወቃቸው ይጠቅማቸዋል ይህንን ሳይዙ ማደጋቸው ግን ምንልባት ዳኛ ሲሆኑ እንኳን በገንዘብ ሊታላሉ ሚዛናዊ ፍርድን ላይፈርዱ ይችላሉ ። በመሆኑም ፍትሃዊነትን ከልጅነታቸው ጅምሮ ማስተማር ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም ። ይህንን ለማስተማር የሚያግዘው ዘዴም በመጽሐፉ ተካቷል እንደ መምህረት እፀገነት ገለጻ።

‹‹በልጆች በኩል ብቻ ሳይሆን በመምህሩም በኩል የምፈልገውን ሀሳብ ምን ያህል አስተላልፌያለሁ የሚለው መመዘን አለበት›› የምትለው መምህርቷ በመጻፉ ባሉት ታሪኮች መጨረሻ ላይ ልጆቹ የሚያደርጉት ተግባር እንዳለም ታወሳለች።

መምህርቷ የህፃናት መፃፉን ልትጽፍ የቻለችው ፈጣን ግንዛቤ የሚያስጨብጡትን የውጭዎቹን መጻፎች የማንበብ ዕድሉን ስላገኘችና የእኛም ሀገር ልጆች በዚህ መንገድ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል መነሳሳትና ከፍተኛ መንፈሳዊ ቅናት ስላደረባት እንደሆነም ትናገራለች። የእኛን ሀገርና የውጭውን የህፃናት መጽሐፍ በንጽጽር ስታየው ርቀቱ ሰፊ እንደሆነ ነው የምትገልፀው። የሕፃናት መፃፍ ሲፃፍ ያለውንና የደረስንበትን የስልጣኔ ደረጃ ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነም ታነሳለች።



በውጭው ዓለም ታዲያ እያንዳንዱ ለህፃናት የሚሆን መጽሐፍ የሚዘጋጀው ጥናትን መሰረት አድርጎ ነውም ትላለች። ሆኖም በእኛ ሀገር ብዙ የህፃናት መጽሐፍትም ሆኑ ሌሎች የማስተማሪያ ግብዓቶች የሚዘጋጁት በፍላጎትና በተነሳሽነት ነው ትላለች። ብዙ ጊዜ በተማሪዎቻችን ላይ ውጤታማነታቸውን ማየት የማንችልበት ምክንያት ይሄው መሆኑንም ታክላለች። መጽሐፍቶቻችንን፤ የምናሳትምበት መንገድን፤ የትምህርት ስርዓቱ፤ የመምህራን የሙያ ጥራት ማስጠበቅ ያልቻልነው በዚህ አካሄዳችን ነው ባይ ናት። አካሄዱ ልጆችን አለማብቃት ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡ ለመምህራን ክብርም እንዳይሰጥ አድርጎታል። ሌላው ቀርቶ ልጆችን ወደፊት ምን መሆን ነው የምትፈልጉት ሲባሉ መምህር እሆናለሁ ብሎ የሚመልስ ጥቂት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ልጆችንም ጨምሮ በጆሯቸው በመስማት በቀላሉ መማር የሚችሉ እንዳሉ ሁሉ በዓይን በማየት በቀላሉ መማር የሚችሉም ብዙ ናቸው። ለምሳሌ በቀላሉ በዓይን መማር የሚችሉትን እንዲያዳምጡ የምናስገድዳቸው ከሆነ ውጤታማ አይሆኑም። ልጆቹ ትምህርቱን እንደ ዕዳ ነው ይቆጥሩታል ‹‹እኔ በግሌ ተማሪ ረባሽ ነው ብዩ አላምንም። የሚረብሸው የሚማረው ነገር ሳያገኝ ሲቀር ነው›› ትላለች።

እንደ እሷ ይሄ የሚሆነው የሚማረው ነገር ወይ ከአቅሙ በታች ወይም ከአቅሙ በላይ ሲሆን ነው። አንድ ክፍል ውስጥ ሆኖ የሚሳተፍበት ነገር ከሌለ መረበሽ የሚሻለው መሆኑን ለአስተማሪው ማሳየት አለበት። አንድ ተማሪ ልጅ የሚረብሸው ደደብ ስለሆነና ስለማይገባው አይደለም። አንድ ክፍል ሆነው የሚሳተፉበት ነገር ከሌለ መረበሽን ይመርጣሉ። ሁላችንም ተመሳሳይ አእምሮ ቢሰጠንም አእምሯችንን የምንሞላበት መንገድ ልክ እንደ ተፈጥሯችን ይለያያል። በመሆኑም በተወሰነ ደረጃ ከፋፍሎ በምን መማር ይችላል የሚለውን ከለየን በኋላ በዚህ መንገድ በማስተማር ልጆቹን ውጤታማ ማድረግ ይቻላል በሚለው በምታስተምርበት ትምህርት ቤትም ሆነ ከባለቤቷ ጋርም ትሰራለች።

ይሄን የ21ኛው ክፍለ ዘመን የማስተማር መንገድ በመደበኛው መንገድ ተምረውና ፈጥነውም ሆነ ዘግይተው ግንዛቤ መያዝ ለማይችሉ በኢትዮጵያ ላሉ ልጆችም አምጥቶ መጠቀም ይቻላል። ባለቤቷና ልጇ በቤት ውስጥ አቅም የሌላቸውን የአካባቢውን ልጆች ሰብስበው በሚያስተምሩበት ወቅት እንዲህ ዓይነት የትምህርት አቀባበል ያላቸው ልጆች ሲገጥሟቸው ለእሷ ሪፖርት ያደርጉላታል።

ለምሳሌ ችግር ሲኖር ይሄም ልጆቹን ቁጭ አድርጎ ለልጆቹ ቃለ መጠየቅ በማድረግ የሚያደርጉት በማየት ልጆቹ ምን ዓይነት ችግር እንዳለባቸው ጥናት ይሰራል።

ብዙዎች የሚያጋጥሟቸው ረጅም ሰዓት ትኩረት ማድረግ ያለመቻል ነው። እንዲህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ልጆች በመደበኛው መንገድ የሚማሩ ልጆች በሚማሩበት መንገድ አስተምሮ ውጤታማ ማድረግ አይቻልም። በመሆኑም ሌላ የተለየ መንገድ መፈለግ ያስፈልጋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ትኩረታቸውን ለማራዘምና ለማስተማር የሚረዱ ሥራዎችን ትሰራለች። ይሄ ታዲያ የተለያዩ የስነ ልቦና ችግር ያለባቸውን ልጆች ለምሳሌ እናትና አባት የተለያዩባቸው እንደገና በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ያሉ ልጆችን ውጤታማ ለማድረግ ይረዳል። ችግሮቹንና ቀውሶቹን ተቋቁሞ ትምህርት ቤት ውሎ ውጤታማ መሆን በጣም የሚከብድበትን ሁኔታ ያቀልላቸዋል። የምታዘጋጀውም የስነ ልቦና ቀውስን ተቋቁሞ እነዚህ ዓይነት ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ግብዓት ነው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከሃምሳና ስልሳ ዓመታት በፊት የታተሙ ጋዜጦች ይዘው የወጡትን ዘገባዎች ያስታውሰናል። የደብረ ዘይት የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት የተለያዩ የእንስሳት በሽታ መከላከያ መድኃኒት እየቀመመ ለእንስሳት ሕክምና በሥራ ላይ ማዋሉ ለትውስታ ከመረጥናቸው ዘገባዎች ተጠቃሽ ነው። ሌሎች በተለይም የመዝናኛ ይዘት ያላቸው ዘገባዎችንም መራርጠን እንደሚከተለው አቅርበናል።

### ለ፷ ሚሊዮን እንስሳት የሚበቃ መድኃኒት ተቀምሟል

ደብረ ዘይት፤(ኢ.ዜ.አ.)፤ ደብረ ዘይት የሚገኘው የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት፤ በዚህ ዓመት ለ፷ ሚሊዮን ፬፻፴፫ሺህ ፳፻፺፰ እንስሳት የሚበቃ ልዩ ልዩ የእንስሶች በሽታ መከላከያ የሚሆን መድኃኒት መቀመሙን አንድ የኢንስቲትዩቱ ቃል አቀባይ ገለጠ።

ቃል አቀባዩ ከዚህ አያይዞ እንዳስረዳው፤ የተቀመመው መድኃኒት ፰ ሚሊየን፫፻፴፰ ሺህ ፪፻ ዶዝ ለቀንድ ከብቶች፣ ለአሳማዎች በሽታ መከላከያ መሆኑን ገልጧል።

እንደዚሁም፤ በተለይ የተዘጋጀ ፓስቴውሪላ ፩፻፸፯ ሺህ ፬፻፳፫ ዶዝ ፣አባ ጎርባ ለተባለው በሽታ መከላከያ፤ ፩፻፸፩ ሺህ ፪፻፶ ዶዝ፣ ለአባ ሠንጋ በሽታ መከላከያ ፬ሺህ ዶዝ፣ ፋውል ታይፎይድ ማለት(የዶሮ በሽታ) ፫ሺህ ፫፻ ዶዝ፣ ፋውል ኮሌራ (የዶሮ) በሽታ መከላከያ የሆኑ መድኃኒቶችን ቀምሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

ቃል አቀባዩ አቶ ጌታሁን አበጀ ከዚህም በማያያዝ፤ ኢንስቲትዩቱ ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ መድኃኒቶችን ቀምሞ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ታድለው በሥራ ላይ መዋላቸውን ከገለጡ በኋላ፤ የመከላከያ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር ስናስመጣ እዚሁ ስለሚቀመምና ስለሚዘጋጅ የከብት ሕክምና ዋና መምሪያ በሽታውን ለመከላከልም ሆነ፤ ፈጽሞ ለማስወገድ በየቦታው ያሠማራቸው ሠራተኞቹ መከላከያ መድኃኒት የማነስም ሆነ የማጣት ችግር አይገጥማቸውም።

የመከላከያ መድኃኒቶቹን በላቦራቶሪ ውስጥ ቀምመው የሚያዘጋጁ አንድ ኢትዮጵያዊ ዶክተርና ሦስት የውጭ አገር ዶክተሮች ይገኛሉ። ከዚህም ሌላ በቂ ትምህርት ያላቸው ቴክኒሺያኖችና የዶክተሮቹ ረዳቶች መኖራቸውን ገልጠዋል።

(ነሐሴ 11ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ፪ ጭንቅላት ያለው ጥጃ ሞቶ ተወለደ

ጎባ (ኢ.ዜ.አ.) በባሌ ጠቅላይ ግዛት በገናሌ አውራጃ በዶዶላ ወረዳ ግዛት አቤና አንሻ በተባለው ቀበሌ ባለፈው ግንቦት ፳ ቀን ፲፱፻፷ ዓ/ም ንብረትነቷ የአቶ ጂሎ ጊጐ የሆነች ላም ልዩ ተፈጥሮ ያለው አንድ ወንድ ጥጃ ወለደች።

ይኸው የተወለደው ጥጃ ሁለት ጭንቅላት፤ ፬ ጆሮ ፤ ሁለት አፍ፤ ፬ ዓይን ሁለት ጭራ ያለው ሲሆን የእበት መጣያ ሥፍራ ደግሞ ድፍን መሆኑ ታውቋል። ጥጃው ከላይ በተጠቀሱት የአካል ክፍሎች ከሌሎች እንስሳት የተለየ ቢሆንም፤ እግሮቹና ብልቱ ትክክለኛውን የእንስሳት ተፈጥሮ የያዙ ናቸው።

ይኸው ልዩ ተፈጥሮ ያለው ጥጃ ከመወለዱ በፊት በእናቱ ማህፀን ሞቶ ስለነበር በመንደር ወጌሻ እርዳታ የወጣ መሆኑን የአውራጃው ግዛት ዋና ጸሐፊ አቶ ሙላት ሙሉነህ ገለጡ።

(ሰኔ 1 ቀን 1961 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ወንዝ ውስጥ ገቡ

የመቶ አለቃ ታደሰ ዱባለ የተባሉ የክቡር ዘበኛ ባልደረባ ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ.ም፤ ከምሽቱ ፫ ሰዓት ከሐያ ደቂቃ ሲሆን፤ የሰሌዳው ቁጥር ፮ሺህ ፰፻፹ የሆነ ሠራዊት ጂፕ መኪና ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኮከብ ወደ ሚያዝያ ፳፯ አደባባይ እየነዱ ሲሔዱ ራስ መኮንን ድልድይ ሲደርሱ፤ ወደ ግራቸው ተጠምዝዘው የድልድዩን ድጋፍ ከሰበሩ በኋላ፤ ወንዝ ውስጥ ገብተው አደጋ ደርሶባቸዋል።

አደጋ መሆኑ እንደተሰማ፤ የትራፊክ ፖሊሶች ከሥፍራው ደርሰው በእሳት አደጋ ወታደሮች ዕርዳታ ቁስለኛውን ከድልድዩ ውስጥ ካወጡ በኋላ፤ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ወስደዋቸው የመጀመሪያ ዕርዳታ ከተደረገላቸው በኋላ ፤ የደረሰባቸው ቁስል ከባድ በመሆኑ ወደ ክቡር ዘበኛ ሆስፒታል ተዛውረው በዚያ ተኝተዋል።

እድልድዩ የገባው ጂፕ ትናንት በክቡር ዘበኛ መኪና ተጐትቶ ከወንዙ ውስጥ ወጥቷል።

(ሐምሌ 7 ቀን 1953 ዓ.ም የወጣው አዲስ ዘመን)

### ኢትዮጵያ በፀጥታ ምክር ቤት መቀመጫ እንዲሰጣት ጠየቀች

ከተባበሩት መንግሥታት ኢትዮጵያና ሞሪታንያ በፀጥታው ምክር ቤት ውስጥ አሁን በተባበረው ዓረብ ሪፑብሊክ የተያዘ የመካከለኛው መሥራቅ (ሥፍራ መቀመጫ) ለእኛ ይገባል ሲሉ ውድድር አቅርበዋል በማለት ከኒውየርክ የተገኘ ወሬ አስታውቋል።

ለምዕራብውያኑ አውሮፓ ክፍልና ለመካከለኛው ምሥራቅ እንዲሆኑ ጠቅላላ ስምምነት ተደርሶባቸው የነበረው መቀመጫዎች፤ ሌሎችም የአፍሪካ አገሮች ለማግኘት በመከራከር ላይ እንደሚገኙ ተገልጿል።

ሌሎች መቀመጫውን ለመያዝ የሚወዳደሩ አገሮች ኢራን ሞሮኮና አፍጋኒስታን እንደሆኑ ታውቋል።

(ነሐሴ 24 ቀን 1954 ዓ.ም. ከወጣው አዲስ ዘመን )

### ዝንጀሮ ሰው በላ

ጅማ፤ (ኢዜአ)፡- በከፋ ጠቅላይ ግዛት በሊሙ ኮሣ ወረዳ ግዛት በርቄ በተባለው ቀበሌ አንድ ዝንጀሮ የ፪ ዓመት ዕድሜ ያለው ወንድ ልጅ መብላቱ ተነገረ።

ዝንጀሮው ሕፃኑን ልጅ ከበላ በኋላ በተጨማሪ አንዲት የ፫ ዓመት ዕድሜ ያላት ልጅ ለመብላት ሲሞክር ሰው ደርሶ አድኗታል። ሆኖም ልጅቷን ለመብላት መሬት ጥሎ በመቦጫጨቅ የመቁሰል አደጋ ያደረሰባት መሆኑ ከቀበሌው መልከኛ ተገልጧል ሲል የወረዳው ግዛት ጸሐፊ አቶ ለማ አዱኛ ገለጡ።

ዝንጀሮው አንዱን ልጅ በልቶ ሌላዋን ልጅ ያቆሰለው ልጆቹ በቤታቸው አቅራቢያ ሲጫወቱ አግኝቷቸው መሆኑን ዋና ጸሐፊው በተጨማሪ አረጋግጠዋል።

ይኸው ዝንጀሮ ልጆቹን ከመብላቱ በፊት፤ ከ፴ ያላነሱ በጐችና ፍየሎች በልቶ ወደ ጫካ እየተሸሸገ የኖረ መሆኑ ታውቋል።

(መስከረም 1 ቀን 1962 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

# ዓለም አቀፍ



## በዩጋንዳ ዳግም የተቀሰቀሰው የኢቦላ ወረርሽኝ የ19 ሰዎች ሕይወት ቀጠፈ

በቅርቡ በዩጋንዳ ዳግም የተቀሰቀሰው የኢቦላ ወረርሽኝ በአጭር ጊዜ ውስጥ የ19 ሰዎች ሕይወት በመቅጠፉ በአገሪቱ ላይ ትልቅ ሥጋት ደቅኗል።

ዩጋንዳ የወረርሽኙ ፍጥነት በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ በአንዳንድ አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማወጅ ተገዳለች። በአገሪቱ በሙቤንዴና በካሳንዳ ወረዳዎች ሆቴሎች፣ የዳንስ ምሽት ክበቦች፣ የአምልኮና የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች እንዲዘጉ ከመደረጋቸው በተጨማሪ ሰው ከቤቱ እንዳይወጣ የጊዜ ገደብ ለመጣል እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ተገልጿል።

የበሽታውን ስርጭት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመግታት በታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሁለቱ ወረዳዎች ከጭነት መኪናዎች ውጭ ምንም ዓይነት የትራንስፖርት እንቅስቃሴ አለመኖሩን ተነግሯል።

የዩጋንዳው ፕሬዚዳንት ዩዌሪ መሴቬኒ ቀደም ሲል በሽታው እንደ ኮሮና ወረርሽኝ በአየር የሚተላለፍ ባለመሆኑ በወረርሽኙ ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና ሌሎች ገደቦች ማስቀመጥ አላስፈላጊ መሆኑን ቢገልጹም፣ በሽታው በአጭር ጊዜ ውስጥ ካጠቃቸው 58 ሰዎች 19 ላይ የሞት አደጋ በማድረሱ በፕሬዚዳንቱ ዘንድ በተፈጠረው ድንጋጤ የአቋም ለውጥ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል።

በወረርሽኙ የተጠረጠረና ወደ ሕሙማን ማቆያ መግባት ፍቃደኛ ያልሆነው ማንኛውም የአገሪቱ ዜጎች ላይ ፖሊስ ጠንካራ እርምጃ እንዲወስድ ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ ትእዛዝ ማስተላለፋቸውንም ቢቢሲ አክሎ ዘግቧል።

ቀደም ሲል በባህላዊ መንገድ ወረርሽኙን ለማከም የተደረገዉ ጥረት ለበሽታው መስፋፋት ሞቹ ሁኔታን በመፍጠሩ በባህላዊ ዘዴ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቆምም ፕሬዚዳንቱ ትእዛዝ ሰጥተዋል።

አሁን ላይ ይፋ የተደረገው የሟቾች ቁጥር 19 ይባል እንጂ ቁጥሩ ከዚያ በላይ ሊሆን እንደሚችል የተነገረ ሲሆን ወረረሽኙ በስፋት የተከሰተባቸው አካባቢዎች ከአገሪቱ ርዕሰ መዲና ከካምፓላ በቅርብ ርቀት ላይ መሆናቸው ደግሞ ሌላ ሥጋት ፈጥሯል።

ኢቦላ ወረርሽኝ እ.ኤ.አ ከ2013 እስከ 2016 በምዕራብ አፍሪካ ብቻ የ11 ሺህ ሰዎች ሕይወት በመቅጠፍ ትልቅ ጠባሳን ጥሎ አልፏል።

ወረርሽኙ የሚተላለፈው ከሰውነት የሚወጡ ፈሳሾች ጋር ንኪኪ በማድረግ እንዲሁም በተበከሉ ቀሳቁሶች ጋር በሚደረግ ንኪኪ ሲሆን ምልክቶቹም ትውከት፣ ተቅማጥ፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ የሰውነት መዛል፣ የጡንቻዎች ህመም፣ የአፍ ምሬት እና የውስጥና የውጭ አካል ክፍሎች መድማት ናቸው። በሽታው ከወባና ከታይፎይድ ጋር ግንኙነት እንዳለውም ተገልጿል።

## እርቃናቸው የተገኙ የስደተኞች ጉዳይ እንዳሳሰበው ተመድ ገለጸ

በግሪክ እና ቱርክ ድንበር ላይ እርቃናቸውን ለመሄድ የተገዱዱ የስደተኞች ጉዳይ እንዳሳሰበው የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ መግለጹን ቢቢሲ አስነብቧል።

92 የሚሆኑ የሶሪያ እና የአፍጋኒስታን ዜጎች በግሪክ እና ቱርክ ድንበር ላይ እርቃናቸውን መገኘታቸው በእጅጉ እንዳሳሰበው የገለጸው፤ ስደተኞቹ እርቃናቸውን በመገኘታቸው ጎረቤታሞቹ ቱርክ እና ግሪክ እርስ በእርሳቸው እየተወቃቀሱ መሆናቸውንም አመልክቷል።

ግሪክ “ለሰው ልጅ ስልጣኔ አሳፋሪ ተግባር” ስትል በድርጊቱ ቱርክን ስትወቅስ ወቅሳለች ቱርክ በበኩሏ የጎረቤቷን የግሪክ ውንጀላ “የሐሰት ዜና” ካለች በኋላ ድርጊቱ “የጭካኔ ተግባር” ስትል ግሪክን ወቅሳለች።

ኤጀንሲው በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ምርመራ እንዲደረግ የጠየቀ ሲሆን “በወጡት አስደንጋጭ ዘገባዎች እና ምስሎች በጣም አዝኛለሁ” ሲል ገልጿል።

የፕሬዚዳንት ሬሲፕ ታይብ ኤርዶጋን ከፍተኛ የፕሬስ ረዳት ፋህረቲን አልቱን በማህበራዊ ድረ-ገጻቸው ላይ “የግሪክ የሐሰት ዜናዎች ማሽን ወደ ሥራው ተመልሷል” ብለዋል።

ክሱን “ከንቱ እና አስቂኝ ነው” በማለት ግሪክ የስደተኞቹን ምስል በማሰራጨት ለስደተኞቹ ክብር እንደሌላት አሳይታለች ሲሉ ወቅሰዋል።

የግሪክ ፖሊስ ዓርብ ዕለት ከቱርክ ጋር በሚያዋስነው ሰሜናዊ ድንበር አቅራቢያ እርቃናቸውን ከተገኙት 92 ስደተኞች መካከል የተወሰኑት ሰውነታቸው ላይ ጉዳት አጋጥሟቸው መገኘታቸውን ይፋ አድርጓል።

በግሪክ ፖሊስ እና በአውሮፓ ሕብረት የድንበር ኤጀንሲ ፍሮንቴክስ በተደረገው ምርመራ ስደተኞቹ የኤቭሮስ ወንዝን በፕላስቲክ ጀልባ አቋርጠው ከቱርክ ወደ ግሪክ እንደገቡ የሚያሳይ ማስረጃ መገኘቱን ፖሊስ አክሏል።

የግሪክ ባለስልጣናት እንዳሉት ስደተኞቹ ግሪክ ከገቡ በኋላ ወዲያውኑ ልብስ፣ ምግብ እና የመጀመሪያ ደረጃ የህክምና እርዳታ አግኝተዋል።

ፍሮንቴክስ ግለሰቦቹ በዋናነት ከአፍጋኒስታን እና ከሶሪያ የመጡ እንደሆኑ እና የመብት ጥሰቶችም ሳያጋጥማቸው እንዳልቀረ ተናግሯል።

የግሪክ የሲቪሎች ጥበቃ ሚኒስትር ታኪስ ቴዎዶሪካኮስ ቱርክ ከጎረቤቶቿ ጋር ያላትን ቅራኔ ለመወጣት “ሕገ-ወጥ ስደትን መሳሪያ አድርጋ ትጠቀማለች” ሲሉ ከሰዋል።

የግሪክ የስደተኞች ጉዳይ ሚኒስትር ኖቲስ ሚታራቺ በትዊተር ገፃቸው ላይ ቱርክ የስደተኞች አያያዟ “ለስልጣኔ አሳፋሪ ነው” ብለዋል። አንካራ ጉዳዩን እንድታጣራ እና “ከአውሮፓ ህብረት ጋር ያላትን ድንበር ትጠብቃለች” ብለው እንደሚጠብቁ ሚንስትሩ ተናግረዋል።

ቱርክ በበኩሏ በጉዳዩ ላይ ምንም ኃላፊነት እንደማትወስድ እና “በኢሰብዓዊ አያያዝም” ግሪክን ተጠያቂ አድርገዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## አዳዲስ የማራቶን ተስፋዎች በአምስተርዳም

**ብርሃን ፈይሳ**

በየዘመኑ ተተኪ የሚሆኑ የአትሌቲክስ ጀግኖችን የምታፈራው ኢትዮጵያ፤ አሁን ደግሞ ከመም ወደ ማራቶን ውድድሮች የተሸጋገሩ አዳዲስ ከዋክብቶችን አግኝታለች። እጅግ ፈታኝ በሆነው የማራቶን ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ ተሳትፈው ውጤታማ የሆኑት ድንቅ ድንቅ አትሌቶችም ከመላው ዓለም አድናቆት እየጎረፈላቸው ይገኛል። ታሪካዊ በሆነውና በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ በተሰጠው የአምስተርዳም ማራቶን በኦሊምፒክና ሌሎች የመም ውድድሮች የለመዱትን በክብር ላይ ክብር መደረብ ደግመው አሳይተዋል። በሁለቱም ጾታ ከተፎካካሪዎቻቸው ልቀው በመገኘት የበላይነቱን በመውሰድ የአገራቸውን ስምም አስጠርተዋል።

ይህ ውድድር አስቀድሞ የተጠበቀው በተለይ በሴቶች በኩል ነበር። ለዚህ ምክንያት የሆነው ደግሞ በረጅምና መካከለኛ ርቀት የመም ውድድሮች የስፖርቱን ቤተሰብ ያስደመሙት ጀግኖች በእኩል ወቅት ፊታቸውን ወደ ማራቶን በማዞራቸው ነው። ስኬታማ እንደሆኑበት የመም ውድድር ሁሉ በጎዳና ላይም ስኬታማ ይሆናሉ የሚለውም በበርካቶች ዘንድ የሚጠበቅ ጉዳይ ነበር። በውድድሩም ላይ በማራቶን ልምድ እንዳላቸው አትሌቶች አብዛኛውን ርቀት ሲመሩ የቆዩት ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ሲሆኑ፤ በግማሽ ማራቶን በተደጋጋሚ በመሮጥ ልምድ ያላት ጸሃይ ገመቹ እስከ 33ኛው ኪሎ ሜትር ድረስ ውድድሩን ስትቆጣጠር ቆይታለች። ከ35 ኪሎ ሜትር በኋላ ግን



**አትሌት አልማዝ አያና በአምስተርዳም ማራቶን ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ አሸናፊ ሆናለች፤**

የሪዮ ኦሊምፒክ ጀግናዋ አትሌት አልማዝ አያና ወደፊት በመስፈንጠር የመሪነቱን ቦታ በመያዝ አሸናፊ ለመሆን ችላለች።

አልማዝ ፍጥነቷን በመጨመርም የርቀቱን የመጨረሻ መስመር በቀዳሚነት ስትረግጥ፤ የገባችበት 2:17:20 የሆነ ሰዓት የአምስርተርዳም ማራቶን ፈጣኑ ሰዓት ሆኖ ተመዝግቦላታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ሶስተኛ ሆና ስታጠናቅቅ በሃምቡርግ ማራቶን ከገባችበት ሰዓት በሶስት ሰከንዶች የፈጠነና የኢትዮጵያን ክብረወሰን የግሏ ለማድረግ ያስቻላት ነው። ከዓለም ደግሞ ሰባተኛው ፈጣን ሰዓት በመሆኑ አትሌቷ የማራቶን ጉዞዋን በስኬት መጀመሯን አስመስክራለች። እአአ የ2016ቱ የሪዮ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትርን ለረጅም ዓመታት ሳይደፈር የቆየውን ክብረወሰን በማሻሻል አድናቆትን ያተረፈችው አልማዝ፤ በ1ሺ500 ሜትር የነሃስ ሜዳሊያ በማጥለቅም ስኬታማ ነበረች። ይሁንና በጉዳትና በወሊድ ምክንያት ለረጅም ጊዜ በውድድሮች ላይ ሳትታይ ቆይታለች።

እአአ የ2015 እና 2017 የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናዎችን በ5ሺ እና 10ሺ ሜትሮች ስኬታማ አትሌት ስትሆን፤ በዓለም አትሌቲክስ የዓመቱ ምርጥ አትሌትነት ተመራጭ መሆኗም የሚታወስ ነው። ከዓመታት በኋላም ባለፈው ወር የግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ ከተሳተፈች በኋላ ማራቶንን ሮጣለች። አትሌቷ ከድሏ በኋላም «ቃላት የለኝም፤ ይህ የተለየ ነገር ነው ደስ ብሎኛል። ከ2016ቱ ኦሊምፒክ በኋላ በጉዳት ምክንያት አስቸጋሪ ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት። በባለቤቴ፤ ልጄ እና በስልጠና ቡድኔ እገዛ ለዚ በቅቻለሁ» በማለት ገልጻለች።

ሌላኛዋ ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ በመሮጥ ስኬታማነቷን ከወዲሁ ያረጋገጠችው ገንዘቤ ዲባባ ናት። አልማዝን ተከትላ በመግባት 2:18:05 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ በመሆን ውድድሩን ያጠናቀቀችው አትሌቷ ከዓለም 20 ምርጥ የማራቶን አትሌቶች መካከል አንዷ ለመሆን የሚያስችላትን ጅምር አሳይታለች። ብርቱ ተፎካካሪ የነበረችውና ሩጫውን ስትቆጣጠር ቆይታ የአገሯ ልጆች አሸናፊዎች እንዲሆኑ ከፍተኛ ሚና የተጫወተችው ጸሃይ ገመቹ ደግሞ ሶስተኛ ደረጃን ይዛለች። 2:18:59 በሆነ ሰዓት የገባችው አትሌቷ ከግማሽ ማራቶን ወደ ማራቶን ያደረገችው ሽግግር በስኬት የታጀበ መሆኑንም አረጋግጣበታለች።

በወንዶች በኩልም ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች አንደኛ እና ሶስተኛ ደረጃን ይዘው በማጠናቀቅ በውድድሩ የነበራቸውን የበላይነት አሳይተዋል። በርቀቱ እስከ 35ኛው ኪሎ ሜትር ድረስ በአሯሯጭ የታገዙት ኬንያውያን አትሌቶች በመሪነት ቢቆዩም ኢትዮጵያውያኑ ብርቱ አትሌቶች ለአምስት ጊዜ በተቀናቃኞቻቸው የተያዘውን የውድድሩን አልሸነፍ ባይነት ሰብረው በማለፍ ለአሸናፊነት በቅተዋል። 40ኛው ኪሎ ሜትር ላይም አትሌት ጸጋዬ ጌታቸው አፈትልኮ በመውጣት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገ ሲሆን፤ 2:04:49 በሆነ ሰዓት በመግባት አሸናፊ ሊሆን ችሏል። ከውድድሩም በኋላ «ጥሩ ውድድር ነበር፤ አየሩም ሆነ ድጋፍ ሰጪዎቹም መልካም ነበሩ» ብሏል።

ኬንያዊው አትሌት ቲቱስ ኪፕሩቶ አሸናፊ ለመሆን ጠንካራ ፉክክር ቢያደርግም በአምስት ሰከንዶች በመዘግየቱ ሁለተኛ ለመሆን ተገዷል። እጅግ ጠንካራ የአሸናፊነት ፉክክር በታየበት ውድድር ሶስት ሰከንዶችን ብቻ በመዘግየቱ ኬንያዊውን አትሌት ተከትሎ የገባው ደግሞ ኢትዮጵያዊው አትሌት ባዘዘው አስማረ ነው። ብርቱው አትሌት ኬንያውያኑ አትሌቶች ቡድን ሰብሮ በመግባት የማሸነፍ ውጥናቸውን ለማክሸፍ ችሏል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ልማት ፎረም የመቋቋም ፋይዳ

**በዳንኤል አበበ**

አርብቶ አደርነት ጥንታዊና የዳበረ ሥልተ ምርትና የኑሮ ዘይቤ ነው። አርብቶ አደር የሚባለው አርብቶ አደርነትን የሚከውን የማኅበረሰብ ክፍል ነው። የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች መኖሪያ 61 በመቶ የሆነውን የአገሪቱን መሬት ይሸፍናል። በአርብቶ አደርነት የሚኖረው ህዝብ ደግሞ ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከ14 እስከ 15 በመቶ ይደርሳል።

በአገራችን የአፋር፣ የሶማሌ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎችን የሚያካትት 220 ወረዳዎች የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ይገኛሉ።

አርብቶ አደሮች የሚኖሩበት አካባቢ በከርሰ ምድርና በገጸ ምድር ውኃ፣ ማዕድናትና የግጦሽ ሀብት የዳበረ ነው። የአገራችን አርብቶ አደሮች ለዘመናት የዳበረ ማኅበረሰባዊና ባህላዊ አስተዳደርና ዕውቀትን በመጠቀም ቁሳዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሀብቶቻቸውን ወደ ምርት ውጤትና ለኑሮአቸው አስፈላጊ የሆኑ የምግብና ገንዘብ ገቢ ምንጭነት የሚለውጡ ጠንካራ ህዝቦች ናቸው።

እ.ኤ.አ. በ2008 በተደረገ ጥናት አርብቶ አደርነት በኢትዮጵያ እስከ 16 በመቶ አጠቃላይ አገራዊ ምርት ያበርክታል። የአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረት የእንስሳት ሀብቱ ሲሆን የቀንድ ከብትን፣ ግመልን፣ በግን፣ ፍየልንና የጋማ ከብትን በዋናነት ያካትታል።

አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢዎች ከአገሪቱ ጠቅላላ የከብት ሀብት 24 በመቶ ያህል ድርሻ እንዳላቸው ቢገመትም፤ በኋላቀር የእንስሳት እርባታ ዘዴ ምክንያት እና በሌሎች ውስጣዊና ውጫዊ



ምክንያቶች አርብቶ አደሩም ሆነ አገራችን ኢትዮጵያ የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ አይደሉም። በአርብቶ አደር አካባቢ የሚኖሩ ወገኖቻችን በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች በተደጋጋሚ የሚጠቁ ናቸው።

አገራችንን በእንስሳት ቁጥር ከአፍሪካ ቀዳሚ ያደረጋት በአርብቶ አደሩ እጅ ያሉ ከብቶች ናቸው። እነዚህ ከብቶች በእንክብካቤ ቢያዙና ህጋዊ የገበያ ስርአት ውስጥ ቢገቡ ለአርብቶ አደሩም ለአገርም ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖራቸው አያከራክርም።

ሰሞኑን ጥቅምት 4 ቀን 2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮችን የእንስሳት ሀብት ልማትና ግብይት፣ ችግሮችን ለመፍታት የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ፎረም በይፋ ተመስርቷል።

በኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ሀሳብ አመንጪነትና አስተባባሪነት የተመሰረተው ፎረሙ በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚታየውን የእንስሳት ሃብት ልማት፣ግብይት፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በተጨባጭ ለመፍታት የግብርና ሚኒስቴር፣ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ፎረሙን በበላይነት ይመሩታል።

በፎረሙ ምስረታ ስነስርዓት ላይ መልዕክት ያስተላላፉት የግብርና ሚኒስትር አቶ ዑመር ሁሴን፤ በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በእንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ ነው። ብለዋል። የእንስሳት ሀብት ልማትን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል በአሥር ዓመቱ የግብርና መሪ ዕቅድ ውስጥ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ይገኛል።

በአርብቶ አደሮች የኑሮ ዘይቤና ባህላዊ ማንነት ላይ መሰረት አድርጎ የተመሰረተ ፎረሙ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ፣ ጠንካራ የገበያ ትስስርና የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ያጠናክራል። ከዚህም በተጨማሪ ሕገወጥ የቁም እንስሳት ንግድና ኮንትሮባንድን ለመግታት ያግዛል።

ፎረሙን በአደረጃጀት የሚመሩት አካላት የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር የፎረሙ ሰብሳቢ፣ የግብርና ሚኒስቴር ምክትል ሰብሳቢ፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን ፀሐፊ፣ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ እንስሳት ባለሙያዎች ማህበር፣ የብሔራዊ ባንክ እና የልማት አጋሮች አባል የሆኑበት ነው።

ፎረሙ በዓመት አራት ግዜ የስራ እንቅስቃሴዎችን ይገመግማል። ውሳኔዎችን ያስተላልፋል። በፎረሙ የተያዙ ስትራቴጂክ እቅዶችን ማጽደቅና በትግበራም ወቅት በአግባቡ መፈጸሙን በከፍተኛ ደረጃ ክትትልና አመራር እንዲሰጥም ይጠበቃል።

በተመሳሳይ ሁኔታ የፎረሙ የመፈጠር ምክንያቶች እንዲሳኩ በፌዴራል፣ በክልል እንዲሁም በዞን ደረጃ የሚገኙት የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተሰላስለው በዋነኛነት በዕቅድ ቀረጻና እቅዱን በመተግበር ሂደት ከሴክተር መስሪያ ቤቶችና ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመተባበር ቁልፍ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

ፎረሙ ገበያ መር ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ አካታች የፋይንናስ አገልግሎትን በማጠናከር እና የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማሻሻል እና በሌሎች ስትራቴጂክ ጉዳዮች ላይ ተጠምዶ በአርብቶ አደሩና በከፊል አርብቶ አደሩ አካባቢዎች ያሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ይፈታል ተብሎ ይጠበቃል። አርብቶ አደሩ ያለውን የእንስሳት ፀጋ ተጠቅሞ ኑሮውን በማሻሻል አገራችን ከዘርፉ እንድትጠቀም የፎረሙ መቋቋም እጅግ አስፈላጊ ነው።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et